የማዕድን ሚኒስቴር
Ministry of Mines
Federal Democratic Republic Of Ethiopia

**የማዕድን ልማት ለኢትዮጵያ ብልጽግና መሠረት!**

# የማዕድን ዘርፍ የ2014 በጀት ዓመት
# የመጀመሪያ ስድስት ወራት ዕቅድ አፈፃፀም ሪፖርት

ጥር/ 2014 ዓ.ም

አዲስ አበባ/ኢትዮጵያ

# ማውጫ

*ድርሞ /Executive Summary/* ..... *3*
መግቢያ ..... 5
የትኩረት አቅጣጫዎች ..... 5
የማዕድንና ነዳጅ ምርት አቅርቦትና ኢንዱስትሪ ድጋፍ ፕሮግራም፤ ..... 13
ዋና ዋና የወጭ ንግድ ማዕድናት በዝርዝ ..... 14
የማዕድንና ነዳጅ ኢንቨስትመንት የአካባቢ ማህበረሰብ ትስስር ፕሮግራም፤ ..... 18
የካፒታል ፕሮጀክቶች አፈፃፀም ..... 19
ትምህርትና ሥልጠና እና አቅም ግንባታ ፕሮጀክት ..... 19
የባህላዊ ማዕድናት አምራቾች አመራረት ማሻሻያ ፕሮጀክት/ASM FORMALIZATION/ ..... 19
የዘርፈ ብዙ ጉዳዮች አፈፃፀም ..... 20
የኮቪድ 19 ተፅዕኖ በዘርፉ ላይ ያስከተለው ጫናና የተወሰዱ እርምጃዎች ..... 21
የክትትልና ድጋፍ ሥራዎች አፈፃፀም ..... 22
የፋይናንስ/የፕሮግራም በጀት/ አፈፃፀም ..... 23
የተቋሙ ኦዲት ግኝት ምልከታ ..... 23
የተቋማዊ ሪፎርም እና የአገልግሎት አሰጣጥ አፈጻጸም ..... 23
ለክልሎች የተሰጠ አቅም ግንባታ ተግባራት ..... 24
ያጋጠሙ ችግሮችና የተወሰዱ የመፍትሄ እርምጃዎች ..... 24
ያጋጠሙ ችግሮች ..... 24
5. ማጠቃለያ ..... 25
አባሪ 1 ..... 27
በ2014 በጀት ዓመት የመጀመሪያ ስድስት ወራት የተሰጡ የማዕድን ኢንቨስመንት ፈቃዶች ..... 27

## ድርሞ /Executive Summary/

የማዕድን ሚኒስቴር የማዕድን መረጃዎች በአግባቡ እንዲሰበሰቡ፣ እንዲጠበቁና ለተጠቃሚዎች እንዲቀርቡ ማድረግ፤ ለማዕድን ፍለጋና ልማት ምቹ ሁኔታ በመፍጠር የማዕድን ኢንቨስትመንትን ማበረታታት፣ በማዕድንና ፔትሮሊየምና ጂኦተርማል ፍለጋና ልማት ለሚሰማሩ የግል ባለሃብቶች ፈቃድ መስጠትና በገቡት ውል መሠረትም ሥራቸውን ማካሄዳቸውንና የክፍያ ግዴታቸውን መፈጸማቸውን መቆጣጠር፣ በባሕላዊና በአነስተኛ ደረጃ የሚመረቱ የከበሩና ጌጣጌጥ ማዕድናት ግብይት ሕጋዊ መስመር እንዲይዝ ማድረግ፤ የማዕድንና ተፈጥሮ ጋዝ ልማትን ለማፋጠን የሚረዱ የምርምርና የማሠልጠኛ ተቋሞችን እንደ አስፈላጊነቱ ማቋቋም በአዋጅ የተሰጡት ስልጣንና ተግባራት ናቸው፡፡

ሚኒስቴር መ/ቤቱ በተለይ በአገር በቀል የኢኮኖሚ ማሻሻያ በተሰጠው ልዩ ትኩረት አገራዊ ተልዕኮዎቹን ለማሳካት በአምስት ፕሮግራሞች ዋና ዋና ተግባራትን ያከናወነ ሲሆን የዘርፉን ተቋማዊ አቅም የመገንባት ፕሮግራም፣ የሥነ-ምድር መረጃን ለልማትና ኢንቨስትመንት የማመንጨት ፕሮግራም፣ የማዕድንና ነዳጅ ኢንቨስትመንትን የማስፋፋትና የማጎልበት ፕሮግራም፣ የማዕድንና ነዳጅ ምርት አቅርቦትና የኢንዱስትሪ ድጋፍ ፕሮግራም እንዲሁም የአካባቢና ማህበረሰብ ትስስርና ፕሮግራም ናቸው፡፡ በበጀት አመቱ የመጀመሪያ ስድስት ወራት በእነዚህ ፕሮግራሞች የተለያዩ ተግባራትን በማከናወን በርካታ ውጤቶች ተመዝግበዋል፡፡
ተቋሙ ለዓለም አቀፍ ኩባንያዎች አገልግሎት የሚሰጥ በመሆኑ ተወዳዳሪ አገልግሎት ለመስጠት፣ የሰራተኞችን የስራ ተነሳሽነትና በጋራ የመስራት ባህል የሚያዳብር፣ የአሰራር ግልፅነትን የሚፈጥርና አገራዊ የዘርፉን ገፅታ የሚገነባ የቢሮ ዕድሳትና የምድረ ግቢ ማስዋብ ሥራዎች ተጠናቀው አገልግሎት እየሰጡ ይገኛሉ፡፡ የዘርፉን የሰው ሃይል ለማብቃት ከሳይንስና ከፍተኛ ትምህርት ሚኒስቴር እንዲሁም ከአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ጋር በመተባር በተመረጡ Mineral engineering, petrochemical engineering, Drilling and Laboratory 44 ተማሪዎች በተጨማሪም በዉጭና በአገር ዉስጥ 4 በድምሩ 48 ተማሪዎች ትምህርት እየተከታተሉ ይገኛሉ፣ አዲስ የማዕድን ኢንቨስትመንት ፈቃዶች በሚመለከት 32 የምርመራ እና 16 የምርት በድምሩ 48 የተሰጡ ሲሆን እነዚህም ለአገር ዉስጥ ባለሀብቶች 12 የምርመራ እና 9 የምርት ፈቃዶች እና ለዉጭ አገር ባለሀብቶች 20 የምርመራ እና 7 የምርት ፈቃዶች ናቸዉ፡፡ በተጨማሪም ለ9 የነዳጅና ነዳጅ ዉጤቶች ማከፋፈያ ኩባንያዎች እና ለ70 የነዳጅ ማደያዎች የብቃት ማረጋገጫ ሠርቲፊኬት ተሠጥቷል፡፡ በነባር የማዕድን ኢንቨስትመንት ብር 0.0486 ቢሊዮን እንዲሁም ብር 0.5406 ቢሊዮን ብር ስራ ላይ ውሏል፡፡
ለውጭ ገበያ ከቀረቡ ማዕድናት በባህላዊ አምራቾችና በኩባንያዎች ወርቅ 4,446.09 ኪ.ግ ወርቅ፣ 46.147 ቶን ታንታለም፣ 5,423.223 ኪ.ግ ጥሬና 200 ኪ.ግ እሴት የጨመረበት ኦፓል፣ 1,688.787 ኪ.ግ የጌጣጌጥ ማዕድናት፣ 3,016 ቶን አዳዲስ የኢንዱስትሪ ማዕድናት ወደ ገበያ እንዲገቡ ተደርጓል፡፡ ለውጭ ገበያ ከቀረቡ ጌጣጌጥና ኢንዱስትሪ ማዕድናት 10.575 ሚሊዮን ዶላር ከወርቅ ማዕድን 272.871 ሚሊዮን ዶላር በድምሩ 283.446 ሚሊዮን ዶላር የዉጭ ምንዛሬ ተገኝቷል፡፡

በክልል ባለፈቃዶች 3.184 ሚሊዮን ቶን የኢንዱስትሪ ማዕድናት ምርት እና 12.7855 ሚሊዮን ሜ.ኪዩብ የኮንስትራክሽን ማዕድናት ምርት ለአገር ዉስጥ ገበያ ቀርቧል፡፡

በዘርፉ ከማዕድን ስራዎች የተሰበሰቡ ልዩ ልዩ ገቢዎችን በሚመለከት በድምሩ ብር 271.332 ሚሊየን ገቢ ተገኝቷል፡፡ የማዕድን ኢንቨስትመንት አካባቢና ማህበረሰቡን ተጠቃሚነት ለማረጋገጥ በበጀት አመቱ 11.496 ሚሊዮን ብር የአካባቢና ማህበረሰብ ልማት ፈንድ መሰብሰብ ተችሏል፡፡

የስራ ዕድል ፈጠራን በሚመለከት በዘርፉ በአጠቃላይ ባለፉት ስድስት ወራት ለ64,407 ዜጎች የሥራ ዕድል ተፈጥሯል፡፡

የኢንቨስትመንት ኩባንያዎች የአቅም ውስንነት፣ በአንዳንድ አካባቢዎች የፀጥታ ችግሮች መከሰት፣ በክልሎች የዘርፉ አደረጃጀት ወጥነት የሌለውና የተሟላ አለመሆን ያጋጠሙ ዋና ዋና ችግሮች ናቸው፡፡

የዘርፉን አቅም በመገንባት ተቋማዊ አገልግሎት አሰጣጥን ማሻሻል፣ ከክልሎችና ሌሎች ባለድርሻ አካላት ጋር ያለውን ትብብርና ትስስር ማጠናከር፣ በውጭ ምንዛሪ ግኝት ላይ ከፍተኛ አስተዋፅኦ እያበረከቱ ያሉትን የባህላዊ ማዕድናት አምራቾች ምርትና ምርታማነት ማጎልበት፣ ለውጭ ገበያ የሚቀርቡ ማዕድናትን በዓይነትና በመጠን ማሳደግ፣ የማዕድንና ነዳጅ ኢንቨስትመንቶች የአካባቢና ማህበረሰብ ተጠቃሚነት ያረጋገጡ እንዲሆኑ ማድረግ፣ በዘርፉ አቅምና ልምድ ያላቸው ኩባንያዎችን እንዲሰማሩ ድጋፍ ማድረግ፣ የእሴት ማበልፀግ ሥራዎች እንዲሁም ዓለም አቀፋዊ ፖለቲካዊ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ጣልቃ ገብነትንና ተፅዕኖን ለመቋቋም ማዕድናት ለአገራዊ ሀብት ማከማቻ እንደ አንድ አማራጭ እንዲያገለግሉ ማድረግ በቀጣይ በልዩ ትኩረት የሚሰራባቸው ናቸው፡፡

# መግቢያ

የማዕድንና ነዳጅ ዘርፍ የአገር በቀል የኢኮኖሚ ማሻሻያው ትኩረት ከሰጣቸው ክፍለ ኢኮኖሚዎች አንዱ ነው፡፡ በቀጣይ ዓመታት ዕውን ለምናደርገው አገራዊ ብልፅግና ከባድ ፈተና እንደሚሆን የሚጠበቀውን የውጭ ምንዛሪ አቅርቦት ለመፍታት የአንበሳውን ድርሻ የመውሰድ አቅም ያለው በመሆኑ ነው፡፡ ከዚህም ባሻገር በቀጥታና በተዘዋዋሪ መንገድ ለሚሊዮኖች የስራ ዕድል መፍጠር የሚችል ከመሆኑም ባሻገር ከውጭ የሚገቡ የኢንዱስትሪና ሌሎች ዘርፎች የማዕድናት ግብዓት ፍላጎትን በአገር ውስጥ ለመተካት የሚያስችል ያልተነካ አገራዊ አቅም አለ፡፡

በመሆኑም ዘርፉ የአገር ውስጥ ኢንዱስትሪዎች እንዲሰፋ ለግብዓትነት የሚያገለግሉ ምርቶችን ማቅረብ እንዲሁም ለአገራዊ ሀብት ማከማቻነት ጉልህ አስተዋፅኦ ማበርከት ይችላል፡፡ ይህ ሪፖርት የማዕድንና ነዳጅ ዘርፍ የ2014 በጀት ዓመት የመጀመሪያ ስድስት ወራት ዕቅድ አፈፃፀም መረጃ ሲሆን የሚኒስቴር መ/ቤቱን፣ የተጠሪ ተቋማቱን እንዲሁም በክልሎች በዘርፉ የተከናወኑ ተግባራትን አፈፃፀም ያካተተ ነው፡፡

ሪፖርቱ በዋና ዋና የውጤት አመላካቾች ወይም (KPI) የተከናወኑና በአገራዊ ፖሊሲ ማትሪክሱ በሚኒስቴር መ/ቤታችን እንዲፈፀሙ የተለዩ ዐቢይ ተግባራትንና ተያያዥ ስራዎችን እንዲሁም የፋይናንስ አፈፃፀም፣ የኦዲት ምልከታ የተቋማዊ ሪፎርም፣ ዘርፈ ብዙ ተግባራት እና ሌሎች መረጃዎችን ያካተተ ነው፡፡

## የትኩረት አቅጣጫዎች

በበጀት ዓመቱ የዘርፉን ውጤታማነት ለማጎልበት በሚከተሉት የትኩረት አቅጣጫዎች የተመራ ነበር፡፡

- የወጪ ንግድ ማዕድናትን በዓይነት፣ በመጠንና በብዛት ለገበያ እንዲቀርቡ በማድረግ የውጭ ምንዛሪ ግኝትን ማሳደግ እንዲሁም ለአገር ውስጥ ኢንዱስትሪዎች የሚያስፈልጉ ማዕድናት በአገር ውስጥ ማድረግ፣
- ዘመናዊ የማዕድናት ግብይት ስርዓት መዘርጋት፣
- በዘርፉ የውጪ ቀጥታ ኢንቨስትመንት ለማሳደግ የሥነ-ምድር መረጃ በጥራትና በሽፋን በማበልፀግ የፕሮጀክት አዋጭነትን የሚያሳዩ የፕሮሞሽን ሥራዎች በአገር ውስጥና በዓለም አቀፍ መዳረሻዎች በስፋት መስራት በመስራት ግዙፍ ኩባንያዎች በዘርፉ ማሰማራት፣
- በዘርፉ የተሰጡ ነባር የማዕድን ልማት ፕሮጀክቶችን ድጋፍና ክትትል በማጎልበት የፕሮጀክቶችን የውል አስተዳዳርና አፈፃፀም ውጤታማ ለማድረግ በትኩረት መስራት፤
- በባለድርሻ አካላት እንዲሁም ከክልሎች ጋር ጠንካራ ቅንጅታዊ አሰራር የመዘርጋት ስራዎችን መስራት፣

➢ ከፍተኛ የማዕድናት ሐብት ባለባቸው አካባቢዎችና አገራዊ ፋይዳቸው በላቁ የማዕድን ኩባንያዎች አካባቢ የሚስተዋሉ የፀጥታ ችግሮች እንዲቀረፉ በልዩ ትኩረት መስራት፣

➢ የዘርፉ የተማረ የሰዉ ኃይል በጥራትና በብዛት እንዲኖር መስራት፣

➢ የኢትዮጵያ ማዕድናት የብራንዲንግ ሥራ በማከናወን ዓለም አቀፍ እዉቅና እንዲኖራቸዉ መስራት፤

# የዘርፉን ተቋማዊ አቅምና ብቃት የማጎልበት ፕሮግራም

**ዓላማ**

ተቋማዊ የመፈጸምና የማስፈጸም አቅም በማሳደግ እንዲሁም ምቹ የሥራ አካባቢን በመፍጠር የማዕድንና ነዳጅ ሥራ ግልጸኝነት የሰፈነበት፤ ዘመናዊነትና ዓለም አቀፍ ተወዳዳሪነት ያለዉ እንዲሆኑ ማድረግ ነዉ፡፡

**የተከናወኑ ተግባራት፡-**

• በቁጥር 6 የዘርፉን ተወዳዳሪነት የሚያጎለብቱ ረቂቅ ፖሊሲዎች፣ አዋጆችና ደንቦች ዝግጅቶችን ማጠናቀቅና ወደ ሥራ ለማስገባት ታቅዶ ፡-

➢ 2 ፖሊሲዎች /የማዕድን እና የነዳጅ/ ረቂቅ ተዘጋጅቶ የነበረ ቢሆንም በአደረጃጀት ለውጥ ምክንያት የተሰጡ ተግባርና ሃላፊነቶችን ማካተቱን ለማረጋገጥ የክለሳ ሥራ በመከናወን ላይ ነው፡፡

➢ 2 አዋጆች ማለትም የማዕድን ሥራዎች አዋጅ ቁ. 678/2002 ቀደም ሲል ከተዘጋጀለት ሁለት ማሻሻያዎች ጋር ተሸሽሎ መዘጋጀት ያለበት መሆኑ በመታመኑ እና የነዳጅ ሥራዎች አዋጅ ቁጥር 295/1978 ከአፍሪካ ልማት ባንክ በተገኘ ድጋፍ የአፍሪካ የሕግ ድጋፍ ሰጪ ተቋም በኩል የመጀመሪያው ረቂቅ ተዘጋጅቶ ውይይት እየተደረገበት ይገኛል፡፡

➢ 2 የተጠሪ ተቋማትን ስልጣንና ተግባር ለመወሰን የሚረዳ ረቂቅ ደንብ ተዘጋጅቶ ለአስተያየት ለፍትህ ሚኒስቴር ተልኳል፡፡

• የተጠሪ ተቋማትን /የማዕድን ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩትን እና የኢትዮጵያ ጂኦሎጂካል ኢንስቲትዩት/ የውስጥ አደረጃጀት የማሻሻል ሥራ ለማከናወን ታቅዶ የተጠሪ ተቋማትን ስልጣንና ተግባር ለመወሰን ረቂቅ ደንብ ተዘጋጅቶ ለአስተያየት ለጠቅላይ አቃቢ ህግ ተልኮ ምላሽ እየተጠበቀ በመሆኑ የውስጥ አደረጃጀት የማሻሻል ሥራ ማከናወን አልተቻለም፡፡

• በኩባያዎች ለሚቀርቡ የፈቃድ ጥያቄዎች የፈቃድ ስምምነት ሰነድ የማዘጋጀት ሥራ የተከናወነ ሲሆን አዋጆች፣ ደንቦች እና መመሪያዎች ለማህበረሰቡ ተደራሽ ማድረግን በተመለከተ፡-

➢ የህግ ማዕቀፋትን የማሻሻል ሥራ እየተከናወነ በመሆኑ ለባለድርሻ አካላት/ ለክልሎች የግንዛቤ ማስጨበጫ ሥራዎች በቀጣይ የሚከናወኑ ይሆናሉ፡፡

➢ ለሚኒስቴር መ/ቤቱ ፣ ለክልል የዘርፉ መ/ቤቶች፣ ለባለፈቃዶች እና ለሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት በሚያቀርቧቸው ጥያቄዎች መሠረት የሕግ ማብራሪያ፣ ምክርና አስተያየት የተሰጠ ሲሆን በሥራ ላይ ያሉ የሕግ ቅጂዎችን ተደራሽ የማድረግ ሥራም እየተከናወነ ይገኛል፡፡

• 14 የተለያዩ የማዕድን ማውጫ ቦታዎች ላይ የፀጥታ ስጋት ለመፍታት ከመከላከያ ሚ/ር፣ ፌዴራል ፖሊስ፣ የደህንነት መረብ ኤጀንሲ እና አርቲፌሻል ኢንተለጀንሲ ሃላፊዎች ጋር ዉይይት በማድረግ የማዕድን ፖሊስ ለማቋቋም የመግባቢያ ስምምነት በመፈራረም ወደ ስራ ተገብቷል፡፡ በመሆኑም የሎጂስቲክስ አቅርቦት ግዥ ተጠናቋል (20 ፓትሮል መኪና ግዥ ተፈጽሟል) ፣ የቦታዎች ሙሉ መረጃ ማፕ ተደርጓል፣ በቦታው የሚገኙ ኩባኒያዎችና የማዕድናት አይነት መረጃ ለጸጥታ አካላት ተሰጥቷል፡፡ በዚህም መሠረት ኦሮሚያ፣ ቤኒሻንጉል፣ ጋምቤላ፣ ደቡብ ምዕራብ ቦታዎች በክልሉ የጸጥታ ሀይሎች ጸጥታ በማስፈን አምራቾችን ወደ ስራ መመለስ ተችሏል፡፡

• የተቋሙን የዉስጥ አደረጃጀት በማጥራት የሰዉ ኃይል ምደባን ሙሉ ለሙሉ ለማጠናቀቅ ታቅዶ የዕቅዱን 90 በመቶ የተከናወነ ሲሆን በዚህም አደረጃጀቱ ተዘጋጅቶ ለሚመለከተው አካል ተልኳል፡፡ ይህ አደረጃጀት ለሚኒስቴር መ/ቤቱ ተጠሪ የሆኑትን በአዲስ መልክ የተደራጁትን የማዕድን ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስትቲዩት እና የኢትዮጵያ ጂኦሎጂካል ኢንስትቲዩት ያሉ የወል ሥራዎችን በፕል እንዲሰራ ተደረጎ የተዘጋጀ ነው፡፡

• የሥራ ተነሳሽነትን የሚያሳድግ ምቹ ቢሮና የሥራ አካባቢ 100% ለመፍጠር ታቅዶ 90% የተከናወነ ሲሆን በዚህም በአዲሱ ህንፃ በሶስተኛ ፍሎር ላይ የትልቁ መሰብሰቢያ አዳራሽ የኮርኒስ ሥራ፣ የመድረክ እንዲሁም የኦዲዮ ቪዥዋል ሥራዎች በመሰራት ላይ ይገኛል፡፡ በአጠቃላይ የ3ኛ ፍሎር የግንባታ ሥራ 85% የደረሰ ሲሆን የAudio visual ሥራው ተሠርቶና ፈርኒቸር ተሟልቶለት በ1 ወር ጊዜ ውስጥ ለሥራ ዝግጁ የሚደረግ ይሆናል:: በዚሁ ፍሎር ትልቁ የመሰብሰቢያ አዳራሽ የግንባታ ሥራ 70% የደረሰ ሲሆን እስከ ጥር መጨረሻ Audio Visual system ተጠናቆ ፈርኒቸር ተሟልቶለት ለሥራ ዝግጁ ይሆናል::

• የማዕድን ኤግዚቢሽን ጋለሪ ማዕከል ሙሉ ለሙሉ ማጠናቀቅ ታቅዶ ግንባታው 60% የደረሰ ሲሆን አስፈላጊው የፊኒሺንግ ማቴሪያል ከውጭ በማምጣት ፈርኒቸር ተሟልቶለት Audio visual system install ተደርጎ እስከ ጥር መጨረሻ የሚጠናቀቅ ይሆናል::

• ዘርፉ ለአገራዊ ኢኮኖሚ የሚያበረክተዉን አስተዋፅኦ ለማወቅ የሚያስችል የጂዲፒ አስተዋፅኦ ጥናት (Sectoral GDP contribution analysis) ሥራ ከሎያ አማካሪ ድርጅት /Loya consulting/ ጋር ውል ተገብቶ ሥራዎች የተሰሩ ሲሆን በዚህም አማካሪው ድርጅት በገባው ውል መሠረት የመጀመሪያውን የጥናት

ሪፖርት ሰነድ አቅርቦ ከሚኒስቴር መ/ቤቱ፣ ከባለድርሻ አካላትና ከክልሎች የሚመለከታቸው የሥራ ሃላፊዎችና ባለሙያዎች በተገኙበት የውይይት መድረክ በመፍጠር ግብዓት ተሰብስቧል፡፡

- የዘርፉን የመፈፀም አቅም ለማጎልበት ከአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ጋር በተደረገ ስምምነት 50 ተማሪዎች በማይኒንግና በፔትሮሊየም የትምህርት ዘርፍ እንዲሁም ለ200 የዘርፉ ባለሙያዎች በውጭና በአገር ውስጥ አጫጭር ስልጠናዎችንና የትምህርት ዕድሎችን ለማመቻቸት ታቅዶ በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ 44 ትምህርታቸውን እየተከታተሉ ሲሆን 2 በሲቪል ሰርቪስ እና 2 በዉጭ አገር 48 ተማሪዎች ትምህርታቸውን እየተከታተሉ ይገኛሉ፡፡
- የሰው ሃብት ልማትና አስተዳደር ሥራዎችን ሲስተም በመጠቀም የተቀላጠፈና ምቹ ለማድረግ ታቅዶ ተግባራዊ ተደርጎ የሰው ሃይል መረጃዎችን ወደ ኮምፒዩተር የማስገባት ስራ ተከናውኗል፡፡
- የመረጃ ዳታ ቤዝን በማበልፀግ በስራ ክፍሎች መካከል የመረጃ ልዉዉጥን የተሳለጠ ለማድረግ የመዝገብ ቤት ዳታ ቤዝ ተዘጋጅቶ መረጃ የማስገባት ሥራ እየተሰራ ሲሆን የማዕድን ምርት ግብይት ሥርዓትን ዘመናዊ ለማድርግ የonline system ተዘርግቶ ለማዕድን ላኪዎች የsingle window ቀልጣፋ አገልግሎት እየተሰጠ ይገኛል፡፡
- ዘርፉን የሚያስተዋውቅ በቁጥር 1 ዘጋቢ ፊልም ተዘጋጅቶ በፋና ብሮድካስቲንግ ኮርፖሬት የተላለፈ ሲሆን በፋና ስቱዲዮ ከዘርፉ ምሁራን ጋርም ውይይት ተደርጓል፡፡
- ለ16 የጂኦሎጂካል ኢንስቲትዩት ባለሙያዎች በIntigrated geological information management system /IGIMS ዙሪያ ሥልጠና ተሰጥቷል፣
- Inter governmental Forum on Mining, Minerals, Metals and Sustainable Development (IGF) በማዕድን ገቢ አስተዳደርና ግብር ላይ ባዘጋጀው የonline ስልጠና ላይ 6 የመ/ቤቱ ባለሙያዎች እንዲሳተፉ ተደርጎ ስልጠናው እየተካሄደ ይገኛል፡፡

## የስነ-ምድር መረጃ ለልማትና ለኢንቨስትመንት የማመንጨት ፕሮግራም

ይህ ፕሮግራም በዋናነት የሚተገበረዉ በኢትዮጵያ ጂኦሎጂካል ሰርቬይ ሲሆን የፕሮግራሙ ዋና ዓላማ መሠረታዊ የጂኦሳይንስ፣ የጂኦኬሚስትሪ፣ የጂኦፊዚክስ እና የሥነ-ምድር አደጋዎችን ጥናት በማካሄድ የሀገሪቱን የልማት ሥነ-ምድር መረጃ ሽፋን፣ ጥራት እና ተደራሽነት በማሳደግ የግብርናን ምርት የሚያሳድጉ እና ለኢንዱስትሪ ግብዓት የሚዉሉ ማዕድናት ፍለጋ ማካሄድ፣ ለመሠረተ ልማት የሚያገለግሉ መረጃዎችን መሰብሰብ እና የዉጭ ምንዛሪ ለማፍራትና ለማዳን የሚያስችሉ ማዕድናት ፍለጋ እና ጥናት ማካሄድ ነዉ። በመሆኑም በ2014 በጀት ዓመት የመጀመሪያ ስድስት ወራት የተከናወኑ ዋና ዋና ዉጤት አመልካች ተግባራትና ግቦች እንደሚከተለዉ ቀርበዋል።

✓ በ2013 የተጠኑ 13 የደለል ወርቅ፣ 5 የኢንዱስትሪ ማዕድናት፣ 4 የጌጣጌጥ የጀምስቶን ማዕድናት፣ 1 የድንጋይ ከሰል እና 4 የብረት አለኝታ ቦታ የካርታ ሪፖርት ጥንቅር ሥራ 100% ተከናውኗል፤ በ2014 ፍለጋና ጥናት ለመስክ ሥራ ጠቀሜታ ያላቸውን መረጃዎች የማሰባሰብ ስራ እየተከወነ ይገኛል ።

✓ በቁጥር 4 በመሠረታዊ ጂኦሳይንስ (በ1፡50,000፣ በ1፡100,000 እና በ1፡1,000,000 መስፈርት) የሥነ ምድር መረጃ ጥናት ማከናወን የዲጅታል ጂኦግራፊክ ቤዝ ማፕ የጂኦሞርፎሎጂ ካርታ ዝግጅትና የቀደምት ስራዎች ጥናት 100% ተከናውኗል።

✓ በ2013 የተጠኑ የስነምድር ዝርዝርና የሪጅናል ቦታዎች መረጃዎችን ካርታና ሪፖርት ማጠናቀቅ በቁጥር 7 ለማከናወን ታቅዶ በዕቅዱ መሠረት ተከናውኗል።

✓የ2013 በጀት ዓመት የተጠኑ የጂኦተርማል ሥራዎች 3 ሪፖርት ለማጠናቀቅ ታቅዶ ካርታና ሪፖርት ማጠናቀር 85% ተጠናቋል።

✓ በወርቅ የግብይት ጣቢያዎች ከወርቅ አቅራቢዎች ጥራቱን የጠበቀ ወርቅ ወደ ባንክ እንዲገባ በቁጥር 4,225 ባር ጥፍጥፍ ወርቅ ላይ ምርመራ ተከናውኗል።

✓በቁጥር 20,157 የናሙና ምርመራ አገልግሎት ለመስጠት ታቅዶ በቁጥር 14,154 (የዕቅዱን 70%) አገልግሎት መስጠት ተችሏል።

✓በቁጥር 5,350 የጂኦሳይንስ መረጃ ለተጠቃሚዎች ለማሰራጨት ታቅዶ 4,176 (የዕቅዱን 78%) ለማሰራጨት ተችሏል።

# የማዕድንና ነዳጅ ኢንቨስትመንት የማስፋፋትና የማጎልበት ፕሮግራም

የፕሮግራሙ ዓላማ የማዕድንና ነዳጅ ሃብት ክምችታችን በተለያዩ አማራጮች በማስተዋወቅ የአገር ውስጥና የውጪ ቀጥተኛ ኢንቨስትመንት በማስፋፋት አዳዲስ ኢንቨስትመንቶች መሳብና ነባር ፕሮጀክቶችን የውል አስተዳደርና አፈፃፀም ስርዓቶችን ማጠናከርና የክትትልና ድጋፍ ሥራዎች ማጎልበት ነው፡፡ የጥራት ደረጃውን የጠበቀ የፕሮሞሽን ሥራ በመሥራት አቅም እና ልምድ ያላቸውን ባለሃብቶች ወደ ዘርፉ በመሳብ የዘርፉ ልማት ለኢኮኖሚው አስተዋፀኦ እንዲያበረክት ማስቻል ሲሆን የተከናወኑ ሥራዎችን እንደሚከተሉት ቀርበዋል፡፡

- በነባር የማዕድን ኢንቨስትመንት ፈቃዶች 3.82 ቢሊዮን ብር ሥራ ላይ እንዲዉል ለማድረግ ታቅዶ ነባር ኩባንያዎች በታቀደዉ መልኩ ኢንቨስት ማድረግ ባለመቻላቸዉ 0.091 ቢሊዮን ብር (የዕቅዱን 2.4%) ሥራ ላይ ዉሏል፡፡
- በቁጥር 10 በማዕድን ዘርፍ ለሚሰማሩ የውጭ ቀጥታ ኢንቨስትመንቶች ፈቃድ ለመስጠት ታቅዶ 27 (የዕቅዱን 270%) ተከናዉኗል፡፡ ከተሰጡ ፈቃዶች ውስጥ 20 የምርመራ እና 7 የምርት ፈቃዶች ናቸው፡፡
- በቁጥር 28 ለአገር ውስጥ ኢንቨስትመንት ፈቃድ ለመስጠት ታቅዶ በቁጥር 21 ፈቃድ (የዕቅዱን 75%) ተሰጥቷል፡፡ በዚህም 13 የምርመራ እና 9 የምርት ፈቃዶች ይገኙበታል፡፡
- ለአዲስ የነዳጅና ነዳጅ ውጤቶች ማከፋፈያ ኩባንያዎች በቁጥር 117 የብቃት ማረጋገጫ ለመስጠት ታቅዶ በቁጥር 79 የብቃት ማረጋገጫ (የዕቅዱን 68%) ተሰጥቷል፡፡
- አዲስ ሥራ ላይ የሚውል የነዳጅ ተቋማትና ኩባንያዎች ብር 2,367 ሚሊዮን የኢንቨስትመንት ካፒታል ለማስመዝገብ ታቅዶ ብር 1,126 ሚሊዮን (የዕቅዱን 48 %) ተከናውኗል፡፡
- በቁጥር 7 በማዕድን ዘርፍ የማማከር አገልግሎት የሙያ ብቃት ማረጋገጫ ሰርተፍኬት ለመስጠት ታቅዶ በቁጥር 5 (የዕቅዱን 71.43%) ተከናውኗል፡፡
- በቁጥር 40 በማዕድን ዘርፍ የማማከር አገልግሎት የሙያ ብቃት ማረጋገጫ ሰርተፍኬት ለማደስ ታቅዶ በቁጥር 15 (የዕቅዱን 71%) ታድሷል፡፡
- በቁጥር 75 የግብይት የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ለመስጠት ታቅዶ በቁጥር 129 (የዕቅዱን 172%) ተከናዉኗል፡፡
- በቁጥር 138,588 (ሴት 57,032 እና ወንድ 97,012) በባሕላዊ ማዕድን ማምረት ዘርፍ የስራ ዕድል ለመፍጠር ታቅዶ ባለዉ የፀጥታ ችግር ምክንያት 61,539 (ሴት 18,698 እና ወንድ 42,841) (የዕቅዱን 44.4%) የስራ ዕድል መፍጠር ተችሏል፡፡
- በቁጥር 761 (ሴት 228 እና ወንድ 533) በኩባንያዎች የማዕድን ልማት ዘርፍ የስራ ዕድል ለመፍጠር ታቅዶ 1,901 (ሴት 570 እና ወንድ 1,331) (የዕቅዱን 249%) ተከናዉኗል፡፡

• በቁጥር 8,000 (ሴት 2400 እና ወንድ 5600) በፔትሮሊየም ልማት ዘርፍ የስራ ዕድል ለመፍጠር ታቅዶ በነዳጅ ተቋማት ብቻ 560 (ሴት 168 እና ወንድ 392) የስራ እድል የተፈጠረ ሲሆን በፔትሮሊየም ልማት ዘርፍ የተፈጠረ የሥራ እድል የለም፡፡

• በሌሎች የድጋፍ ዘርፍ በቁጥር 2500 (ሴት 750 እና ወንድ 1750) የሥራ ዕድል ለመፍጠር ታቅዶ በቁጥር 407 (ሴት 122 እና ወንድ 285) (የዕቅዱን 16.3%) ለመፍጠር ተችሏል፡፡

**• በአጠቃላይ በዘርፉ 150,099 (ሴት 45,030 እና ወንድ 105,069) የሥራ ዕድል ለመፍጠር ታቅዶ በቁጥር 64,407 (ሴት19,322 እና ወንድ 45,085) (የዕቅዱን 42.9%) ለመፍጠር ተችሏል፡፡**

• በክልሎች በባህላዊ/ ኢንተርፕራይዝ በቁጥር 3,772 ፈቃዶች ለመስጠት ታቅዶ በቁጥር 2,106 ፈቃዶች (የዕቅዱን 56%) መስጠት ተችሏል፡፡

• የማዕድንና ነዳጅ ሃብት ለውጭ ባለሃብቶች ለማስተዋወቅ የፕሮሞሽን ሰነድ በትብብር ለማዘጋጀት ታቅዶ 1 አጠቃላይ የማዕድን ኢንቨስትመንት ፖቴንሺያልን በተመለከተ እንዲሁም 1 የኮፐር- ሊቲየም- ፖታሽ- ብረት ማዕድናት ፖቴንሺያልን የሚመለከት የፕሮሞሽን ሰነድ ተዘጋጅቷል፡፡

• የብረት ማዕድን በየዓመቱ ከ950 ሚሊዮን ዶላር በላይ ወጪ በማድረግ ከውጭ የሚገባውን ለመተካት (Import substitution) ማዕድኑ በሚገኝባቸው አካባቢዎች የተደረጉ ጥናቶችን በማሰባሰብ ዝርዝር መረጃውን የማደራጀት ስራ የተከናወነ ሲሆን የብረት ማዕድንን በሀገር ውስጥ ምርት ለመተካት የሚያስችል የክምችት መጠን መኖሩን፣ ማዕድኑን በአንድ ማዕከላዊ አካባቢ (centralized) ወይም በየምርት አካባቢው ፕሮሰስ በማድረግ spong Iron/Pig Iron ለማምረት የሚያስፈልገው የኢንቨስትመንት መጠን እና አዋጭነት ጥናት በትብብር እየተዘጋጀ ይገኛል፡፡

• የድንጋይ ከሰልን የሚጠቀሙ ኢንዱስትሪዎች በዓመት የሚያወጡትን 275 ሚሊዮን ዶላር ለማስቀረትና ምርቱን በሀገር ውስጥ ለመተካት የሀገራችንን የድንጋይ ከሰል የክምችት መጠን፣ የጥራት ደረጃውን፣ መገኛ ቦታ፣ የጥራት ደረጃውን ከፍ ለማድረግ የሚያስፈልገውን ቴክኖሎጂ እና የሚፈጀውን የኢንቨስትመንት መጠን የሚያሳይ የአዋጭነት ጥናት በመስራት አዋጭነቱን ለማወቅ የተቻለ ሲሆን በርካታ የሀገር ውስጥ ባለሀብቶችን በመጋበዝ የማስተዋወቅ ስራ ተከናውኗል፡፡

በተጨማሪም የገንዘብና የቴክኒክ አቅም ያላቸውን እንዲሁም ፋብሪካ በመገንባትና በማዕድን ዘርፍ ላይ ልምድ ያላቸውን ኩባንያዎች በተቀመጠው መስፈርት መሰረት በመምረጥ አስፈላጊ ሰነዶችን (ዝርዝር የአዋጭነት ሰነድ፣ የገንዘብ አቅም ማሳያ ፣የኩባንያ ሕጋዊ ሰነዶች፣ የማሽን ግዥ ለማድረግ የተሰበሰበ ፕሮፎርማ ኢንቮይስ፣የፋብሪካ ግንባታ ፈቃድ) እና የመሳሰሉትን ማሟላት የቻሉትን 8 ኩባንያዎች በመለየት ለዚሁ የድንጋይ ከሰል ምርትና ፕሮሰሲንግ ሥራ ፈቃድ ለመስጠት የስምምነት ሰነድ፣ አጭር የፕሮጀክት መግለጫ እና የኩባንያዎችን ፕሮፋይል ሰነድ በማዘጋጀት ለፍትሕ ሚኒስቴር እና ለሚኒስትሮች ምክር ቤት በመላክ እንዲጸድቅ የተደረገ ሲሆን በቀጣይ ስምምነት የሚፈፀም ይሆናል፡፡

- የዕብነበረድ እሴት መጨመርን አስመልክቶ በአሶሳ ከተማ 18 ኩባንያዎች የሚሳተፉበት አሶሳ ማርብል ኢንዱስትሪያል ፓርክ የማቋቋም ስራ እየተሰራና በአሶሳ ዩኒቨርስቲ የስልጠና ማዕከል ለማቋቋም ስምምነት ላይ ተደርሷል፡፡ እሴት የመጨመር ክህሎት ስልጠና በጣልያን ሀገር የሚሰልጥኑ ሰልጠኞችን የመለየት እና ለዚህም ድጋፍ Italian Aid Corporation ጋር በመተባበር ጣሊያን ሀገር ልኮ የአሰልጣኞች ስልጠና ለማካሄድ እየተሰራ ይገኛል፡፡
- በሲሚንቶ አምራች ኢንዱስትሪ ዘርፍ ኩባንያዎች ያሉባቸዉን ችግሮች በመስክ ጉብኝት ጭምር በመለየትና አምራቾችን በማወያየት ሰፊ ስራ የተከናወነ ሲሆን ኩባንያዎች በጥሬ ዕቃ አቅርቦት ችግር፣ በቴክኒካል ኤክስፐርቶች እጥረት፣ በመለዋወጫ ችግር፣ በግብይት ሰንሰለቱ ላይ በሚፈጠር ችግር እና መሠል ተግዳሮቶች በሙሉ አቅማቸዉ ማምረት አለመቻላቸዉን የገለፁ ሲሆን የቴክኒካል ኤክስፐርቶችን ችግር ለመፍታት በአገር ዉስጥ ገበያ የማይገኙትን ከዉጭ አገር በማስገባት እንዲሰሩ ፈቃድ አግኝተዋል፣ የመለዋወጫ ችግሮችን አስመልክቶ በአገር ዉስጥ ብረታ ብረት አምራቾች ችግሩ እንዲቀረፍላቸዉ እና በአገር ዉስጥ የማይገኙትን ደግሞ ከዉጭ እንዲያስገቡ ሁኔታዎችን የማመቻቸት ስራ ተሠርቷል፣ የጥሬ ዕቃ አቅርቦትን በሚመለከት በዘላቂነት ችግሩ የሚፈታበትን ህጋዊ አማራጭ ይዘዉ በመቅረብ ችግሩ እንደሚፈታላቸዉ መስማማት ላይ ተደርሷል፣ በተጨማሪም የግብይት ሂደቱ ላይ ያለዉን አላስፈላጊ ሰንሰለት በማስወገድ ግልጽ የግብይት ሂደት እንዲኖር የሚያደርጉ ተግባራት ተከናዉነዋል፡፡ በዚህም የሲሚንቶ ዋጋን ከነበረበት የአንድ ኩንታል መሸጫ ዋጋ ከብር 900 በአማካይ ወደ ብር 450 ማውረድ እንዲሁም የኩባንያዎችን ዕለታዊ የማምረት አቅም ማሳደግ የተቻለ ሲሆን አጠቃላይ የሲሚንቶ ምርት መጠን በቀን 160,000 ቶን ወደ 240,000 ቶን ለማሳደግ እየተሠራ ነው፡፡
- በተጨማሪም የሲሚንቶ ምርታማነትን ለማሳደግ ኢስት ሲሚንቶ ኩባንያ ላለፉት አራት አመታት ዕገዳ ተጥሎበት የቆየ ሲሆን ዕገዳው ተነስቶ ወደ ሥራ እንዲገባ ተደርጓል፡፡ ናሽናል ሲሚንቶ እና ኢትዮ ሲሚንቶ በህግ ወጥ ሠፋሪዎች እና ካሳ ክፍያ ጋር በተያያዘ የገጠማቸዉ ችግር እንዲፈታ ተደርጓል፡፡

# የማዕድንና ነዳጅ ምርት አቅርቦትና ኢንዱስትሪ ድጋፍ ፕሮግራም፤

በዘርፉ በተሰማሩ ባለሀብቶችና በክልሎች በሚከናወኑ የማዕድናትን፤ የነዳጅና የተፈጥሮ ጋዝ እንዲሁም ባዮፊዩል ምርት ሥራዎች ለገበያ እንዲቀርቡ ድጋፍ ለማድረግ በዚህም ሂደት የሚፈጠሩ ልዩ ልዩ የአገር ዉስጥ ገቢዎችን እና የወጪ ንግድ ማዕድናትን በመሸጥ የሚገኙ የዉጭ ምንዛሪ ገቢዎችን ለማሳደግ የተቀረፀ ፕሮግራም ነዉ፡፡

**የተከናወኑ ተግባራት፡-**

**ለውጪ ገበያ የቀረቡ ማዕድናትን በተመለከተ፡-**

- 1,995.48 ኪ.ግ ወርቅ በኩባንያ ተመርቶ ለገበያ ለማቅረብ ታቅዶ 1,449.3 ኪ.ግ (የዕቅዱን 72.6%) ማቅረብ ተችሏል፡፡
- 5,004.5 ኪ.ግ ወርቅ በባህላዊ አምራቾች ለገበያ ለማቅረብ ታቅዶ 2,996.792 ኪ.ግ (የዕቅዱን 59.7%) ማቅረብ ተችሏል፡፡
- 2,320 ሜ.ኩብ የዕምነበረድ ማዕድናት ምርት ለገበያ ለማቅረብ ታቅዶ በቤንሻንጉል ጉሙዝ ክልል በካማሽ ዞንና አካባቢዉ በተከሰተው የፀጥታ ችግር በዕብነበረድ ምርት ላይ ያሉ ኩባንያዎች ማምረት አለመቻል እንዲሁም በምርት ቦታቸው ያለውን ምርታቸውን አውጥተው ወደ ውጭ ሀገር ገበያ መላክ ባለመቻሉ አፈፃፀም አላሳየም፡፡
- 1,760.5 ኪ.ግ የጌጣጌጥ ማዕድናት ምርት ለዉጭ ገበያ ለማቅረብ ታቅዶ 1,688.787 ኪ.ግ (የዕቅዱን 95.9%) ማቅረብ ተችሏል፡፡
- 871.5 ቶን ኢንዱስትሪ ማዕድናት ምርት ለዉጭ ገበያ ለማቅረብ ታቅዶ 3,016.9 ቶን (የዕቅዱን 346%) ማቅረብ ተችሏል፤
- 50 ቶን ታንታለም በባህላዊ አምራቾች ለዉጭ ገበያ ለማቅረብ ታቅዶ 46.147 ቶን (የዕቅዱን 92.3%) ማቅረብ ተችሏል፤
- 2,750 ኪ.ግ ሌሎች በከፊል የከበሩ የጌጣጌጥ ማዕድናት (ኦፓል በጥቅል) ምርት ለዉጭ ገበያ ለማቅረብ ታቅዶ 5,507.072 ኪ.ግ (የዕቅዱን 200%) ማቅረብ ተችሏል፡፡
- 1,000 ቶን ሶዲየም ብሮማይድ በኩባንያዎች ተመርቶ ለውጭ ገበያ ለማቅረብ ታቅዶ 921 ቶን (የዕቅዱን 92.1%) ማቅረብ ተችሏል፡፡
- **በበጀት ዓመቱ የመጀመሪያ ስድስት ወራት ከማዕድናት ምርት ሽያጭ አጠቃላይ 526 ሚሊዮን ዶላር የውጪ ምንዛሪ ገቢ ለማግኘት ታቅዶ 283.446 ሚሊዮን ዶላር (የዕቅዱን 54%) ተገኝቷል፡፡**

# ዋና ዋና የወጭ ንግድ ማዕድናት በዝርዝ

| ተ.ቁ | የወጪ ምርት ዓይነት | መለኪያ | የ2014 በጀት ዓመት ዕቅድ | የ2014 በጀት ዓመት ስድስት ወራት ዕቅድ | የ2014 በጀት ዓመት ስድስት ወራት ክንውን | የዕቅድ አፈጻጸም በመቶኛ |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | በኩባንያና በባህላዊ አምራቾች የተመረተ የወርቅ መጠን | | | | | |
| 1.1 | ወርቅ በኩባንያ | ኪ.ግ | 3,991 | **1,995.48** | 1,449.3 | |
| የተገኘ ገቢ በሚሊዮን ዶላር | | በሚ.ዶላር | 293.52 | 146.75 | 71.002 | |
| 1.2 | ወርቅ በባህላዊ | ኪ.ግ | 10,009 | **5,004.5** | 2,996.792 | |
| የተገኘ ገቢ በሚሊዮን ዶላር | | በሚ.ዶላር | 736.0710 | 368.04 | 201.869 | |
| | አጠቃላይ ከወርቅ የተገኘ የዉጭ ምንዛሪ በሚ.ዶላር | በሚ.ዶላር | 1029.57 | 257.576 | 272.871 | |
| 2 | ጌጣጌጥና ሌሎች የኢንዱስትሪ ማዕድናት በኪ.ግ/በቶን | | | | | |
| 2.1 | ጥሬ ኦፓል | ኪ.ግ | 5100 | 2550 | 6739.905 | |
| የተገኘ ገቢ በሚሊዮን ዶላር | | በሚ.ዶላር | 1.716 | 0.858 | 1.7374 | |
| 2.2 | እሴት የተጨመረበት ኦፓል | ኪ.ግ | 400 | 200 | 83.85 | |
| የተገኘ ገቢ በሚሊዮን ዶላር | | በሚ.ዶላር | **5.367** | **2.68** | **0.9236** | |
| 2.3 | ኤመራልድ | ኪ.ግ | 480 | 240 | 414.52 | |
| | የተገኘ ገቢ በሚሊዮን ዶላር | በሚ.ዶላር | 0.48 | 0.24 | 0.52 | |
| 2.4 | polished non opal | ኪ.ግ | | | 51.791 | |
| | polished non opal የውጪ ምንዛሪ | በሚ.ዶላር | | | 0.025 | |
| 2.5 | Sclupted Hand Made Stone Chair መጠን | ኪ.ግ | | | 610 | |
| | Sclupted Hand Made Stone Chair መጠን የውጪ ምንዛሪ | በሚ.ዶላር | | | 0.08 | |
| 2.6 | Derbesha emeraled | ኪ.ግ | | | 3.513 | |
| | Derbesha emeraled የውጪ ምንዛሪ | በሚ.ዶላር | | | 0.022 | |
| 2.7 | ሳፋየር | ኪ.ግ | 60 | 30 | 2.122 | |
| | የተገኘ ገቢ በሚሊዮን ዶላር | በሚ.ዶላር | 0.006 | 0.03 | 0.021 | |

| ተ.ቁ | የወጪ ምርት ዓይነት | መለኪያ | የ2014 በጀት ዓመት ዕቅድ | የ2014 በጀት ዓመት ስድስት ወራት ዕቅድ | የ2014 በጀት ዓመት ስድስት ወራት ክንውን | የዕቅድ አፈጻጸም በመቶኛ |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 2.5 | ኢንዱስትሪያል ኳርትዝ | ኪ.ግ | 2000 | 1000 | 357.4 | |
| | የተገኘ ገቢ በሚሊዮን ዶላር | በሚ.ዶላር | 0.84 | 0.42 | 0.149788 | |
| 2.6 | ጀም ኳርትዝ | ኪ.ግ | 0 | 0 | 34.31 | |
| | የተገኘ ገቢ በሚሊዮን ዶላር | በሚ.ዶላር | 0 | 0 | 0.0012 | |
| 2.7 | ክሪስቶጸሬዝ | ኪ.ግ | 30 | 14 | 4 | |
| | የተገኘ ገቢ በሚሊዮን ዶላር | በሚ.ዶላር | 0.00022 | 0.000103 | 0.00002 | |
| 2.8 | ጋርኔት | ኪ.ግ | 60 | 30 | 2.48 | |
| | የተገኘ ገቢ በሚሊዮን ዶላር | በሚ.ዶላር | 0.0018 | 0.0009 | 0.000102 | |
| 2.9 | ቶርማሊን | ኪ.ግ | 400 | 200 | 0.74 | |
| | የተገኘ ገቢ በሚሊዮን ዶላር | በሚ.ዶላር | 0.08 | 0.0402 | 0.000432 | |
| 2.10 | አጌት | ኪ.ግ | 650 | 325 | 122.942 | |
| | የተገኘ ገቢ በሚሊዮን ዶላር | በሚ.ዶላር | 0.005 | 0.00252 | 0.0101 | |
| 2.11 | አሚተስት | ኪ.ግ | 10 | 4.98 | 0 | |
| | የተገኘ ገቢ በሚሊዮን ዶላር | በሚ.ዶላር | 0.00005 | 0.0000249 | 0 | |
| 2.12 | አኳማሪን | ኪ.ግ | 12 | 6 | 16 | |
| | የተገኘ ገቢ በሚሊዮን ዶላር | በሚ.ዶላር | 0.003 | 0.0015 | 0.007348 | |
| 2.13 | አማዞናይት | ኪ.ግ | 110 | 55 | 0.0265 | |
| | የተገኘ ገቢ በሚሊዮን ዶላር | በሚ.ዶላር | 0.0016 | 0.00078 | 0.000247 | |
| 2.14 | ሩቢ( ኮሮንደም) | ኪ.ግ | 200 | 100 | 1.527 | |
| | የተገኘ ገቢ በሚሊዮን ዶላር | በሚ.ዶላር | 0.06 | 0.03 | 0.000381 | |
| 2.15 | ሞርጋናይት | ኪ.ግ | 800 | 400 | 20.38 | |
| | የተገኘ ገቢ በሚሊዮን ዶላር | በሚ.ዶላር | 0.0288 | 0.0144 | 0.00162 | |
| 2.16 | አምበር | ኪ.ግ | 300 | 150 | 5.518 | |
| | የተገኘ ገቢ በሚሊዮን ዶላር | በሚ.ዶላር | 0.075 | 0.0375 | 0.0225 | |
| 2.17 | ማንጋኔዝ | በኪ.ግ | 120 | 70 | 450 | |
| | የተገኘ ገቢ በሚሊዮን ዶላር | በሚ.ዶላር | 0.24 | 0.014 | 0.0675 | |

| ተ.ቁ | የወጪ ምርት ዓይነት | መለኪያ | የ2014 በጀት ዓመት ዕቅድ | የ2014 በጀት ዓመት ስድስት ወራት ዕቅድ | የ2014 በጀት ዓመት ስድስት ወራት ክንውን | የዕቅድ አፈጻጸም በመቶኛ |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 2.18 | ክሮማይት | በቶን | 36 | 12 | 793 | |
| | የተገኘ ገቢ በሚሊዮን ዶላር | በሚ.ዶላር | 0.00063 | 0.00021 | 0.2106 | |
| 2.19 | ቤሪል | በኪ.ግ | 76.4 | 38.2 | 57.28 | |
| | የተገኘ ገቢ በሚሊዮን ዶላር | በሚ.ዶላር | 0.1121 | 0.037 | 0.00000135 | |
| 2.19 | ኢንዱስትሪያል ቤሪል | በኪ.ግ | 76.4 | | 126 | |
| | የተገኘ ገቢ በሚሊዮን ዶላር | በሚ.ዶላር | 0.1121 | | 0.1685 | |
| 2.20 | ስትርን | በኪ.ግ | 500 | 155 | 4 | |
| | የተገኘ ገቢ በሚሊዮን ዶላር | በሚ.ዶላር | 0.0015 | 0.000357 | 0.000032 | |
| 2.21 | ሶዲየም ብሮማይድ(ብሮሚን) | በቶን | 2200 | 1000 | 921 | |
| | የተገኘ ገቢ በሚሊዮን ዶላር | በሚ.ዶላር | 7.92 | 3.6 | 2.759 | |
| 2.22 | ቤንቶኔት | በቶን | 50000 | 25000 | 0 | |
| | የተገኘ ገቢ በሚሊዮን ዶላር | በሚ.ዶላር | 0.05 | 0.0252 | 0 | |
| 2.23 | ሲልካ ሳንድ | በኪ.ግ | | 50 | 0 | |
| | የተገኘ ገቢ በሚሊዮን ዶላር | በሚ.ዶላር | | 0.0075 | 0 | |
| 2.24 | ለውጭ ሀገር ገበያ የሚቀርብ የአርተፍሻል ጌጣጌጦች ምርት መጠን | በኪ.ግ | 4419.04 | 209.52 | 335.334 | |
| | የተገኘ ገቢ በሚሊዮን ዶላር | በሚ.ዶላር | 0.0.9 | 0.045 | 0.1019 | |
| 2.26 | ባዛልት | በቶን | | | 45 | |
| | የተገኘ ገቢ በሚሊዮን ዶላር | በሚ.ዶላር | | | 0.00225 | |
| 2.27 | አሞሌ ጨው | በቶን | | | 0.482 | |
| | የተገኘ ገቢ በሚሊዮን ዶላር | በሚ.ዶላር | | | 0.0025 | |
| 2.28 | ኦብስዲያ | ኪ.ግ | | | 1.2 | |
| | የተገኘ ገቢ በሚሊዮን ዶላር | በሚ.ዶላር | | | 0.0000024 | |
| 2.29 | ፍሎራይት | ኪ.ግ | | | 1.1 | |
| | የተገኘ ገቢ በሚሊዮን ዶላር | በሚ.ዶላር | | | 0.000012 | |
| 2.30 | ኒኬል | በቶን | 300 | 100 | 1045 | |
| | የተገኘ ገቢ በሚሊዮን ዶላር | በሚ.ዶላር | 0.41 | 0.014 | 0.1617 | |
| 2.31 | ኮፐር | በቶን | 300 | 100 | 200 | |
| | የተገኘ ገቢ በሚሊዮን ዶላር | በሚ.ዶላር | 0.1712 | 0.043 | 0.096 | |

| ተ.ቁ | የወጪ ምርት ዓይነት | መለኪያ | የ2014 በጀት ዓመት ዕቅድ | የ2014 በጀት ዓመት ስድስት ወራት ዕቅድ | የ2014 በጀት ዓመት ስድስት ወራት ክንውን | የዕቅድ አፈጻጸም በመቶኛ |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 2.30 | በባህላዊ ተመርቶ ለዉጭ ገበያ የቀረበ ታንታለም | በቶን | 100 | 50 | 46.147 | |
| 2.31 | ከታንታለም የተገኘ የዉጭ ምንዛሪ | በሚ.ዶላር | | 3.408 | 3.4563 | |
| 2.32 | እብነበረድ | በሜ.ኩብ | 5000 | 2284 | 0 | |
| | ከእብነበረድ የተገኘ የዉጭ ምንዛሪ | በሚ.ዶላር | | 0.441 | 0 | |
| ከተለይዩ ጌጣጌጥና ኢንዱስትሪ ማዕድናት የተገኘ የውጭ ምንዛሪ በጥቅል | | በሚ.ዶላር | 10.5751 | | | |
| **አጠቃላይ ከወርቅ፣ ከጌጣጌጥ፣ ከኢንዱስትሪ እና ከመሳሰሉት ማዕድናት የተገኘ የውጭ ምንዛሬ** | | **በሚ.ዶላር** | **1054** | **527** | **283.446** | |

**ለአገር ውስጥ ገበያ ለግብዓትነት የሚቀርቡ ማዕድናት መጠንና ገቢ ማሳደግን በሚመለከት የተከናወኑ ተግባራት፡-**

✓ 3.2 ሚሊየን ቶን የኢንዱስትሪ ማዕድናት ምርት ለሀገር ውስጥ ገበያ ለማቅረብ ታቅዶ 3.184 ሚሊዮን ቶን (የዕቅዱን 99.2%) ማቅረብ ተችሏል፤

✓ 23.01 ሚሊዮን ሜ.ኩብ የኮንስትራክሽን ግብዓት ማዕድናት ምርት ለሀገር ውስጥ ገበያ ለማቅረብ ታቅዶ 12.7855 ሚሊዮን ሜ.ኪብ (የዕቅዱን 55.56%) ማቅረብ ተችሏል፡፡

✓ የጨው ምርት ጥራትና መጠን በመጨመር ለምግብ ፍጆታም ሆነ ለኢንዱስትሪዎች ግብዓት ከውጭ የሚገባውን ሙሉ በሙሉ በመተካት 100% ፍጆታን ለማሟላት ታቅዶ የጨው ማቀነባበሪያ ፋብሪካ ተከላው በሂደት ላይ በመሆኑ ምርቱ ቢመረትም ለኢንዱስትሪዎች ግብዓት የሚሆን ተወዳዳሪ ምርት ማቅረብ ባለመቻሉ አፈፃፀም አላሳየም፡፡

✓ ከፔትሮሊየም ከመሬት ኪራይና ከስልጠና 1.75 ሚሊዮን ዶላር ተሰብስቧል፡፡ ከዚህም 956,760.72 ዶላር የመሬት ኪራይ እና 793,561.64 ዶላር የስልጠና ክፍያ ነው፡፡

✓ ከማዕድን የሚገኝ የሮያሊቲ ገቢ ብር 252.66 ሚሊዮን ለመሰብሰብ ታቅዶ ብር 87.7 ሚሊዮን (የዕቅዱን 34.7%)፣ ከናሙና አገልግሎት ክፍያ ብር 0.0036 ሚሊዮን ለመሰብሰብ ታቅዶ ብር 0.00124 ሚሊዮን (የዕቅዱን 34.4%) እና ከፈቃድ ማውጫ፣ ከመመዝገቢያ፣ ከማደሻ እና ከሙያ ብቃት ክፍያ ብር 0.88 ሚሊዮን ለመሰብሰብ ታቅዶ ብር 4.225 ሚሊዮን (የዕቅዱን 480%)፣ ከግብይት ብቃት ማረጋገጫ ብር 0.05 ሚሊዮን ለመሰብሰብ ታቅዶ ብር 0.038 ሚሊዮን (የዕቅዱን 76%) **በድምሩ በሚኒስቴር መ/ቤቱ በኩል ብር 253.6 ሚሊዮን ለመሰብሰብ ታቅዶ ብር 92.024 ሚሊዮን** (የዕቅዱን 36.3%) ተሰብስቧል፡፡

✓ በክልሎችና ከተማ አስተዳደሮች ከማዕድን ስራዎች የሚሰበሰብ ልዩ ልዩ ገቢ 284 ሚሊዮን ብር ለመሰብሰብ ታቅዶ 179.308 ሚሊዮን ብር (የዕቅዱን 63.1%) ተሰብስቧል፡፡

✓ 125,000 ቶን ጨው፣ 208,126 ቶን ባዛልት፣ 22,462.8 ቶን ሽክላ አፈር፣ 86,986 ቶን ጂብሰም፣1,911,597 ቶን ላይምስቶን እና 41,625 ሜ.ኩብ ዕምነበረድ ለሀገር ውስጥ ገበያ ለማቅረብ ታቅዶ 687.48 ቶን ጨው (የዕቅዱን 0.5%)፣ 113,420 ቶን ባዛልት (የዕቅዱን 54.5%)፣ 34,748.3 ቶን ሽክላ አፈር (የዕቅዱን 155%)፣ 31,624.8 ቶን ጂብሰም (የዕቅዱን 36%)፣1,016,723 ቶን ላይምስቶን ፣(የዕቅዱን 53%) እና 103,945.4 ሜ.ኩ ዕምነበረድ ፣(የዕቅዱን 249.7%) ማቅረብ ተችሏል፡፡ በተጨማሪም 10 ቶን ሶዳሽ እና 7,737 ቶን ሳንድ ስቶን ለአገር ውስጥ ገበያ ቀርቧል፡፡

✓ ለአገር ውስጥ ገበያ ከቀረቡ የተለያዩ ማዕድናት 506.34 ሚሊዮን ብር የሽያጭ ገቢ ለማግኘት ታቅዶ 290.2 ሚሊዮን ብር (የዕቅዱን 94.31%) ገቢ ማግኘት ተችሏል፤

## የማዕድንና ነዳጅ ኢንቨስትመንት የአካባቢ ማህበረሰብ ትስስር ፕሮግራም፤

**ዓላማ**

የባለፈቃዶችን የስራ ጤንነትና ደህንነት አፈጻጸም በመከታተል በማዕድን ልማት አካባቢና በማህበረሰብ ላይ ሊደርሱ የሚችሉትን አሉታዊ ተፅዕኖዎች እንዲቀንሱ እንዲሁም በልማቱ አካባቢ የሚኖሩ ማህበረሰብ ከልማቱ ተጠቃሚ እንዲሆኑና ልማቱን ከአካባቢ ጥበቃና የማህበረሰብ ፍላጎት ጋር የተጣጣመና ዘለቄታዊ ማድረግ ነው፡፡

**የተከናወኑ ተግባራት፡-**

- ከማዕድን እና ነዳጅ አልሚዎች በዉል ስምምነት መሠረት 32 ሚሊዮን ብር ለመሰብሰብ ታቅዶ 11.496 ሚሊዮን ብር (የዕቅዱን 35.9%) ተሰብስቧል፡፡
- ከማዕድን እና ነዳጅ አልሚዎች በዉል ስምምነት መሠረት ከተሰበሰበ የማህበረሰብ ልማት ፈንድ 10 ሚሊዮን ብር ለክልሎች ለማሰራጨት ታቅዶ 0.97 ሚሊዮን ብር ለማሰራጨት ተችሏል፡፡ አፈፃፀሙ ሊቀንስ የቻለዉ
- በ50 የማዕድንና የፔትሮሊየም ኢንቨስትመንት ሥራ ፈቃዶች ከአካባቢ ብክለት የፀዳ እንዲሆን ክትትልና ድጋፍ ለማድረግ እንዲሁም የዘርፉ ኢንቨስትመንት ከአካባቢ ብክለት የፀዳና ከጉዳት ያገገመ እንዲሆን 25 ሄክታር ቦታ በአረንጓዴ ልማት ለመሸፈን ታቅዶ በጸጥታ ምክንያት አልተከናወነም፡፡
- ከCESO-CIRDI ጋር በመተባበር ለ105 የሚኒስቴር መ/ቤቱና የክልል ባለሙያዎች በማህበረሰብ ልማት ዙሪያ ስልጠና ተሰጥቷል፡፡

## የካፒታል ፕሮጀክቶች አፈፃፀም

በ2014 በጀት ዓመት 2 ፕሮጀክቶች ተቀርፀውና ከመንግስት ግምጃ ቤት በጀት ተመድቦላቸው ወደ ሥራ የተገባ ሲሆን በዚህም በበጀት ዓመቱ በመጀመሪያ ስድስት ወራት የተከናወኑ ሥራዎች እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

## ትምህርትና ሥልጠና እና አቅም ግንባታ ፕሮጀክት

ከአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ጋር በተደረገ ስምምነት ለ50 ከክልልና ከተጠሪ ተቋማት ለተውጣጡ ባለሙያዎች በማዕድንና ፔትሮሊየም የትምህርት መስክ የትምህርት ዕድል ለማመቻቸት ታቅዶ ለ44 ባለሙያዎች ዕድሉ ተሰጥቶ ትምህርታቸውን እየተከታተሉ ሲሆን 6 ባለሙያዎች በተለያየ ምክንያት የዕድሉ ተጠቃሚ ሊሆኑ አልቻሉም፡፡

## የባህላዊ ማዕድናት አምራቾች አመራረት ማሻሻያ ፕሮጀክት/ASM FORMALIZATION/

**የተከናወኑ ተግባራት**

- ለባህላዊና አነስተኛ ማዕድን አምራቾች የፈቃድ ቦታ መከለል (Establishing ASM Zone) /በኦሮሚያ፣በደቡብ፣ በቤንሻንጉልና ጋምቤላ/ ታቅዶ ለልዩ አነስተኛ አምራቾች በክልል ፈቃድ ሰጭዎች በኩል የመከለል ስራዉ የተከናወነ ሲሆን የባህላዊ አምራቾችን በሚመለከት መረጃዎችን የማጥራት ስራዎች ተከናዉነዋል፡፡
- በባህላዊና አነስተኛ ደረጃ ማዕድን ማምረት ላይ የተሰማሩ ዜጎችን ሁሉን አቀፍ አቅም በስልጠና ለመገንባት/በተለይ ወርቅና ጌጣጌጥ በብዛት በሚመረትባቸዉ ክልሎች/ ታቅዶ አምስት ቡድኖች ተዋቅረዉ በ5 ክልሎች በመላክ በምርትና ምርታማነት እንዲሁም በግብይት ሂደት ሰፊ የግንዛቤ ማስጨበጫ ስልጠናዎች ተሠጥቷል፡፡
- በተጨማሪም የወርቅና ሌሎች ማዕድናት ህገ-ወጥ ንግድን በመቆጣጠር ምርቱ በብዛት በሚመረትባቸው በጋምቤላ፤ በቤኒሻንጉል፤ በደቡብ፣ በደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ እና በኦሮሚያ ክልሎች ከሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ፣ ከክልልና ከወረዳዎች በተውጣጣ ባለሙያዎች ድጋፍና ክትትል እየተደረገ ነው፡፡
- የሚኒስቴር መ/ቤቱ ከፍተኛ እና መካከለኛ አመራሮች ወደ ወርቅ አምራች ክልሎች በመሄድ ከክልል ፕሬዝዳንቶች፣ ከካቢኔዎቻቸውና ከፖሊስ ኮሚሽነሮች ጋር በማዕድናት ምርት አካባቢ ሠላም እና ፀጥታ በሚከበርበት ሁኔታ እና የኤክስፖርት ምርቶችን መጠን ማሳደግ በሚቻልበት ሁኔታ ዙሪያ ሰፊ ውይይት በማድረግ ከስምምነት ተደርሶ በጋራ ሥራ ተጀምሯል፡፡
- በተመረጡ ወርቅ አምራች ክልሎች ጠበቅ ያለ የምርት ክትትል እና ድጋፍ ተደርጓል፡፡

- በማዕድናት ምርት እና ግብይት ላይ የሚያገጥሙ ችግሮችን በቅርበት በመከታተል እና በመፍታት የተሻለ ሥራ መስራት የተቻለ ሲሆን በዚህም ለተመረጡ ወርቅ አምራች ክልሎች የሎጂስትክ ድጋፍ ተደርጓል፡፡
- በወጪ ንግድ ማዕድናት ሀገራዊ ጥቅም ዙሪያ ለባህላዊ አምራቾች፣ አዘዋዋሪዎችና ለሚመለከታቸው የዘርፍ ሃላፊዎች ግንዛቤ ተፈጥሯል፡፡
- ከዚህን በፊት በጌጣጌጥ ማዕድናት ላይ ተጥለው የነበሩ እግዶችን በማንሳት እና ትክክል ያልሆኑ የጌጣጌጥ ማዕድናት የዋጋ ተመንን የማስተካከል ሥራ ተሰርቷል፡፡
- የወርቅ የባህላዊ አምራቾችን ለማበረታታት ከክልል ፕሬዝዳንቶች ጋር በመነጋገር ከዚህ በፊት በወረዳዎች ይሰበሰብ የነበረ የሮያሊት ክፍያ እንዲነሳላቸው ተደርጓል፡፡
- ምርትና ምርታማነትን ለማሳደግ የባህላዊ አምራቾች አደረጃጀት ማስተካከል አስፈላጊ ሆነ ስለተገኘ ከክልሎች ጋር በመተባበር የbaseline ሥራ እየተሰራ ይገኛል፡፡
- የፀጥታ ሀይልን ለማሰማራት ሚኒስቴር መሳሪያ ቤቱ 20 ፓትሮል መኪኖችን ከውጭ ሀገር ገዝተው ወደ ሀገር ውስጥ ያስገባ ሲሆን በየክልሉ በፓይለትነት በተመረጡ ወረዳዎች ላይ አስፈላጊውን የፀጥታ ስራ ለመስራት በዝግጅት ላይ እንገኛለን፡፡

## የዘርፉ ብዙ ጉዳዮች አፈፃፀም

- ሴት ሠራተኞች ምቹ የሥራ ሁኔታ ተፈጥሮላቸው በሙሉ አቅማቸው በሥራቸው የላቀ ውጤት እንዲያስመዘግቡ ብሎም ጤናማና ፍሬያማ ህብረተሰብ ለማፍራት እንዲያስችል በሚኒስቴር መ/ቤቱ የህፃናት ማቆያ ለማቋቋም ዝርዝር ፕሮፖዛል ተዘጋጅቷል፡፡

- በOcupational health and safety (OHS) and Community Health and Safety impacts assessments and mitigation measures, በCommunity Development, Social management approaches and Community Development Agreement, በAdministerative procedures, practices, methods and approches እንዲሁም በGender Equality in the Mining Sector and Implementation of Gender Knowledge Products ዙሪያ ሥልጠና ተሰጥቷል፡:
- በሥርዓተ ፆታ ጉዳይ ላይ የcapacity assessment Survay በሃረር፣ በድሬዳዋ፣ በሱማሌና በአዲስ አበባ ተከናውኗል፡፡
- በኤችአይ ቪ/ኤድስ እንዲሁም በሕይወት ክህሎት ዙሪያ IEC/BCC ማቴሪያሎችን በማዘጋጀት ለተቋሙ ሠራተኞች ተደራሽ እንዲሆን ተደርጓል፡፡
- ከተቋማት፣ ከሲቪክ ማህበራት እና ሌሎች አካላት ከሚገኝ ድጋፍ እና ከሠራተኛ ከሚዋጣው የኤድስ ፈንድ በሚገኝ ገንዘብ ኤች.አይ.ቪ በደማቸው ለሚገኝ ሠራተኞች እንዲሁም ወላጆቻቸው

በኤች.አይ. ቪ/ኤድስ ምክንያት ወላጆቻቸውን ላጡ እና ለተጋላጭ ህፃናት ድጋፍና እንክብካቤ ተደርጎል፡፡

## የኮቪድ 19 ተፅዕኖ በዘርፉ ላይ ያስከተለው ጫናና የተወሰዱ እርምጃዎች

- የኮቪድ 19 ኮሮና ወረርሽን አለም አቀፋዊ ስጋትነት እና በዘርፉ የልማት እንቅስቃሴ ላይ ያሳደረዉን አሉታዊ ተፅዕኖ ምክንያት በማድረግ የመቋቋሚያ ዕቅድ በማዘጋጀት ወደ ስራ ተግብቷል፣
- በዚሁም ዕቅድ መሠረት በ2013 በጀት ዓመት ተከታትሎ ተግባራዊ በመደረጉ ከፍተኛ ዉጤት የተገኘ ሲሆን በ2014 በጀት ዓመትም በአዲስ መልክ ዕቅዱን የመከለስ ስራ ተሰርቷል፣
- በዕቅዱ መሠረት በየስራ ክፍሉ የግንዛቤ ማሳደጊያ ስራዎችን ከማከናወን ጎን ለጎን የማስክና ሳኒታዘር አጠቃቀም ላይ ክትትል ተደርጓል፣
- ይህንኑ የግንዛቤ ማሳደግ ስራዎች ለዘርፉ ተዋናዮች ተደራሽ ለማድረግ እየተሰራ ነዉ፣
- የመከላከያ እርምጃዎችን (ክትባት መከተብ፣ ንጽህናን በዉሀ እና በሳኒታይዘር የመጠበቅ፣ ማስክን አዘዉትሮ መጠቀም እና ለዚሁ አገልግሎት አቅርቦትን የማረጋገጥ ስራዎች) በቀጣይነት ተግባራዊ የማድረጉ ስራ በዕቅዱ መሠረት እየተከናወነ ይገኛል፡፡

**በካናዳ መንግስት ትብብርና ድጋፍ በሚኒስቴር መ/ቤቱ እየተከናወኑ ያሉ ፕሮጀክቶች አፈፃፀም**

**የSUMM ፕሮጀክት አፈፃፀም**

- የProject Management Unit (PMU) አባላት በተገኙበት የፕሮጀክት አፈጻጸምና የበጀት ዓመቱን ዕቅድ ግምገማ ተካሂዷል፡፡
- የProject Steering Committee (PSC) አባላት በኦንላይን በመገናኘት የፕሮጀክቱን የ5ኛ ዓመት ዕቅድ አፈጻጸምና የ6ኛ ዓመት ዕቅድ በመወያየትና በመገምገም እንዲጸድቅ ተደርጓል:: አስፈላጊ የሆኑ እንደ ቀረጥ ነጻ ያሉ ድጋፎችም ተሰጥቷል፡፡
- ለካዳስተር አገልግሎት የሚውል የ96 ኮምፒዩተሮች፣ የ26 Router, የ 1 ባለ 86" እና 2 ባለ65" LED screen smart TV ግዥ ተከናውኖ አብዛኛው ለክልሎች የተሰራጨ ሲሆን ለMineral Excellence Center የላቦራቶሪ ዕቃዎች ግዥ እየተከናወነ ነው፤
- የካዳስተር አጠቃቀምን በተመለከተ ቱቶሪያል ቪዲዮዎች ተዘጋጅቷል፣
- በተመረጡ ወረዳዎች ላይ ASM Formalizationን ለመተግበር ለተላኩ ባለሙያዎች ድጋፍ ተደርጓል፤
- ለሚኒስትር መ/ቤቱና ለተጠሪ ተቋም ባለሙያዎች የተለያዩ ሥልጠናዎች የተሰጠ ሲሆን በሚኒስቴር መ/ቤቱ ለሚካሄዱ የስብሰባዎችና የስልጠና ፕሮግራም ድጋፍ ተደርጓል፡፡

በአጠቃላይ የሰም ፕሮጀክት መጠናቀቂያ ዓመት ላይ ያለ በመሆኑ ቀሪ የተለያዩ መሳሪያዎች ግዥ፣ ስልጠናዎች እና ሌሎች በዕቅድ የተካተቱ ሥራዎች ወቅቱን ጠብቀው እንዲከናወኑ ክትትል እየተደረገ ይገኛል፡፡

**የSTEM ፕሮጀክት አፈፃፀም**

- የSTEM ፕሮጀክት በ4 ዩኒቨርሲቲዎች እና 2 TVET በአቅም ግንባታ ላይ ሲሰራ የነበረ ሲሆን በግማሽ ዓመቱ ውስጥ በነበረው የጸጥታ ችግር በትግራይ ክልል ለሚገኙት ዩኒቨርሲቲዎችና TVET ሊያደርግ የሚገባውን የአቅም ግንባታ ስራ ባለማከናወኑ በምትኩ በሌሎች ዩኒቨሲቲዎች እንዲሰሩ አማራጮች ቀርቦ የነበረ ቢሆንም የፕሮጀክቱ ዓላማ አይደለም በሚል ተቀባይነት አላገኘም፡፡ ነገር ግን አሁንም አማራጭ በመፈለግ በአማራና በኦሮሚያ ክልል ከሚገኙ የTVET ተቋማት ጋር ለመስራት ወደ ክልሎቹ በመሄድ ግብዓቶች ተሰብስበዋል፡፡ ውጤቱንና አጠቃላይ የቀጣይ ዓመት የስራ ዕቅዳቸውን እንዲያቀርቡ ተደርጎ የፕሮግረስ ሪፖርት አቅርበው በግምገማ ሂደት ላይ ነው፡፡

- ፕሮጀክቱ በኮቪድና ትግራይ በነበረው የጸጥታ ችግር ምክንያት መስራት የነበረበትን ያህል ያልሰራ ሲሆን በትግራይ ለሚገኙ 2 ዩኒቨርሲቲዎች የላቦራቶሪ ዕቃዎችና የመማሪያ ቁሳቁሶች ግዥ ተፈጽሞ ስለመሳሪያዎቹ ዕውቀት ያላቸው ባለሙያ ከውጭ ሃገር እንዲመጣና እንዲያሳይ በሂደት ላይ ነው፡፡ አማራጭ የስራ ፕሮግራም እንዲያቀርቡ ተጠይቀው የስራ ፕሮግራሙ ተዘጋጅቶ በካናዳ ኤምባሲ እየታየ ይገኛል፡፡

## የክትትልና ድጋፍ ሥራዎች አፈፃፀም

**የተከናወኑ ተግባራት፡-**

- የተጠሪ ተቋማትን፣ የክልሎችን እንዲሁም የሚኒስቴር መ/ቤቱን የሥራ ክፍሎች የሥራ አፈፃፀም ሪፖርትና ዕቅዳቸውን በወቅቱ ጥራቱን በጠበቀ መልኩ እንዲያቀርቡ እና የዕቅድ አፈፃፀማቸዉን እንዲያሻሽሉ የድጋፍና ክትትል ሥራ ተሰርቷል፡፡
- የዘርፉ ከፍተኛ አመራሮች የተሳተፉበት በዋና ዋና ማዕድናት የሚመረቱባቸዉ ክልሎች በመገኘት እየተከናወኑ ያሉ ተግባራት የመከታተልና የመደገፍ ስራ ተከናዉኗል፣
- ምርት ያቆሙ ኩባንያዎች ወደ ሥራ እንዲመለሱ እየተደረገ ይገኛል፡፡
- የዓለምን ዕለታዊ የወርቅ ዋጋ በመከታተል አምራች ማህበራትና አቅራቢዎች ወቅታዊ መረጃ እንዲደርሳቸው ተደርጓል፡፡
- የኤሌክትሮኒክስ የአንድ መስኮት አገልግሎት ሥርዓት በሥራ ላይ ዉሏል፡፡

## የፋይናንስ/የፕሮግራም በጀት/ አፈፃፀም

በበጀት ዓመቱ ለመደበኛና ለካፒታል ሥራዎች ከመንግስት ግምጃ ቤት ብር 95 ሚሊዮን ጸድቆ ወደ ሥራ የተገባ ሲሆን እንዲሁም ለዓለም አቀፍ ግልግል ዳኝነት ቀሪ ክፍያ ብር22.81 ሚሊዮን፣ ለህንፃ እድሳት ብር 15.00 ሚሊዮን እና ለመኪና ግዥ ብር 48.87 ሚሊዮን በድምሩ 86.68 ሚሊዮን ተጨማሪ በጀት ፀድቆ በድምሩ ብር 181.68 ሚሊዮን በጀት ተመድቦ ሥራዎች እየተከናወኑ ሲሆን ከዚህም በበጀት ዓመቱ ስድስት ወራት ለመደበኛና ለካፒታል ሥራዎች ከመንግስት ግምጃ ቤት ብር 87.055 ሚሊዮን ሥራ ላይ ዉሏል። ከዚህም ውስጥ ብር 17.35 ሚሊዮን ብር ለዓለም አቀፍ ግልግል ዳኝነት  እንዲሁም ብር 48.87 ሚሊዮን ለመኪና ግዥ የወጡ ወጪዎች ትልቁን ድርሻ ይዘዋል።

## የተቋሙ ኦዲት ግኝት ምልከታ

- ተቋማዊ አሰራሩ ዜሮ የኦዲት ግኝቶች ለማድረስ በልዩ ትኩረት እየተሰራ ነው።
- የክትትል ኦዲት በማድረግ እርምጃ ያልተወሰደባቸው የብር 454,821.29 የኦዲት ግኝቶች ላይ እርምጃ ለመውሰድ በሂደት ላይ ነው።
- የቱሉ ካፔ ኩባንያዎችን የወጪ ይመዝገብልኝ ጥያቄ አዋጁና መመሪያዉ በሚያዘዉ መሠረት ኦዲት ተደርጎ ተገቢነት የሌላቸዉ ብር30.66 ሚሊዮን ብር የመንግስት ወጪ ለማዳን ተችሏል።
- የያራ ዳሎል የወጪ ይመዝገብልኝ ጥያቄ የኦዲት ውጤት ተሰርቶ የብር 2,143.11 ሚሊየን የወጪ ሰነዶች ምርመራ ተደርጎ ብር 106.45 ሚሊዮን የመንግስት ወጪ ማዳን ተችሏል።
- በፖ.ሊ.ጂ.ሲ.ኤል የቀረበ የወጪ ይመዝገብልኝ ጥያቄ የምርመራ ዶክመንት ተዘጋጅቶ ኦዲት እየተደረገ ይገኛል።
- ግምት ያልወጣላቸው በስቶር የሚገኙ ንብረቶች ግምት ወጥቶላቸው እንዲወገዱ ሃሳብ ቀርቦ ውሳኔ እንዲሰጥበት ተደርጓል።

## የተቋማዊ ሪፎርም እና የአገልግሎት አሰጣጥ አፈጻጸም

በተቋማዊ የሪፎርም ሥራዎቻችን የማዕድንና ነዳጅ ዘርፍ በአገር በቀል የኢኮኖሚ ማሻሻያዎች የተሰጠውን ልዩ ተልዕኮ እንዲያሳካ ተቋማችን ውጤታማ የሪፎርም ተግባራትን እያከናወነ ይገኛል። አላቂ የሆነውን የተፈጥሮ ሀብታችን ለዘላቂ የህዝባችን ጥቅምና የአገራችን ብልፅግና ጉዞ መሰረት እንዲሆን እንዲሁም ሃብቱን የማስተዳደርና የመምራት ተቋማዊ ብቃታችን ለማጎልበት በርካታ ተግባራት እየተከናወኑ ይገኛሉ።

ሚኒስቴር መስሪያ ቤታችን ዓለም አቀፍ ልምድና ተሞክሮ ላካበቱ ኩባንያዎችና ኢንቨስተሮች አገልግሎት የሚሰጥ በመሆኑ ከአጋር ድርጅቶች በተገኘ የገንዘብ ድጋፍ እና ከመንግስት ግምጃ ቤት ተጨማሪ በጀት በመጠየቅ ተቋማዊ የአገልግሎት አሰጣጣችንን የሚያዘምኑ ቴክኖሎጂዎችን እያጎለበትን ሲሆን የሰራተኞችን የስራ ተነሳሽነት የሚጨምሩና በጋራ የመስራት ባህልን የሚያዳብሩ፣ የስራ ላይ ደህንነታቸውን የሚያረጋግጥ የቢሮ እድሳትና የምድረ ግቢ ማስዋብ ተግባራት ተጠናቀዉ አገልግሎት

በመስጠት ላይ ነው፡፡ ተቋማዊ መረጃዎችና ሰነዶችን ዲጂታላይዝ የማድረግና ለአጠቃቀም ግልፅ፣ ምቹ፣ ቀላልና ተደራሽ እንዲሆኑ የማድረግ ስራዎች እየተከናወኑ ነው፡፡ በተጨማሪም ባሳለፍነዉ በጀት ዓመት ለዘርፉ ዉጤታማ አፈፃፀም የጎላ ድርሻ ለነበራቸዉ ድርጅቶች፣ አመራሮች፣ ባለሙያዎችና ድጋፍ ሰጭዎች መስፈርት አዘጋጅቶ በመምረጥ የማበረታቻ ሽልማት ተሰጥቷል፡፡

## ለክልሎች የተሰጠ አቅም ግንባታ ተግባራት

የማዕድን ሥራ በባህሪው በዋናነት በክልሎች የሚከናወን በመሆኑ ከክልሎች ጋር በቅንጅት፣ በጋራ ተጠቃሚነት እና በመደጋገፍ መስራት በልማት ዕቅዱ የተቀመጡ የዘርፉን ግቦች ለማሳካት ከፍተኛ ጠቀሜታ አለው፡፡ የማዕድናት ሃብት በስፋት ከሚገኝባቸው አፋር፣ አማራ፣ ኦሮሚያ፣ ቤኒሻንጉል ጉሙዝ፣ የደቡብ ብሄር ብሄረሰቦችና ህዝቦች፣ ጋምቤላና እና ሌሎች ክልሎች ጋር በጋራ ተጠቃሚነት መርህ በመስራት በዘርፉ የሚስተዋሉ ችግሮችን ለመቅረፍ የክልል ከፍተኛ አመራሮችን በማሳተፍ ገንቢ ውይይቶችና ቅንጅታዊ አሰራሮች እንዲዘረጉ በስፋት የተሰራ ሲሆን በእነዚህና በሌሎች ስራዎቻችን አበረታች ውጤቶች ተገኝተዋል፡፡

- የክልሎችን ተጠቃሚነት የሚያጎለብቱ ሁለት ፕሮጀክቶች (ASM formalization and Capacity building Projct) ፀድቀዉ ወደ ስራ የገቡ ሲሆን በዚህም የባህላዊ አምራቾችን እና የክልል፣የዞንና የወረዳ ፈፃሚዎችን አቅም በመገንባት በተለይ የከበሩና በከፊል የከበሩ ማዕድናት ላይ ምርትና ምርታማነታቸዉን ለማሳደግ እንደሚያግዝ ታምኖበታል፣

- ለተመረጡ ክልሎች በመረጃ አያያዝ፣ በፈቃድ አሰጣጥና አስተዳደር እንዲሁም ህገወጥነትን በመከላከል ዙሪያ የግንዛቤ ማስጨበጫ ስራዎች ተከናዉነዋል፡፡
- በ5 ክልሎች (ኦሮሚያ፣ ብኒሻንጉል ጉሙዝ፣ ጋምቤላና ደቡብ ብ/ብ/ህ፣ ደቡብ ምዕራብ ክልል) የወርቅ ምርት በብዛት በሚመረትባቸዉ ፓይሌት ወረዳዎች በመምረጥ የባህላዊ አምራቾችን ምርትና ምርታማነት የማሳደግና የግብይቱን ህጋዊነት የማረጋገጥ ስራዎች በ5 ቡድን በተደራጁና እያንዳንዳቸዉ ከሚ/ር መ/ቤቱና ከክልሎች በተዉጣጡ ቡድኖች እየተከናወነ ይገኛል፡፡
- በSUMM ፕሮጀክት የተገዙ ኮምፕዩተሮችና መሠል ቁሳቁሶች (Computers with accessories) ለኦሮሚያ (ጉጂ ዞን) ድሬዳዋ፣ ሶማሊ፣ ሲዳማ፣ ደቡብ፣ ጋምቤላ እና ሀረሪ ክልሎች ተሰራጭቷል፡፡

## ያጋጠሙ ችግሮችና የተወሰዱ የመፍትሄ እርምጃዎች

### ያጋጠሙ ችግሮች

- በማዕድናት ማምረቻ ቦታዎች የሚስተዋል የፀጥታ ችግር፣
- የኩባንያዎች በሚፈለገዉ መልኩ ወደ ሥራ አለመግባት፣
- የሠራተኞች የመፈፀም አቅም ዉስንነት፣

➢ አንዳንድ ቁልፍ ተግባራት አሁን ባለዉ ሁኔታ ሊፈፀሙ የሚችሉ አለመሆናቸዉ እና ማስተካከልም አለመቻሉ ዋና ዋናዎቹ ናቸዉ፡፡

## የተወሰዱ የመፍትሄ እርምጃዎች

• የተለያዩ የማዕድን ማውጫ ቦታዎች ላይ የሚስተዋለዉን የፀጥታ ችግር ለመፍታት ከመከላከያ ሚ/ር፣ ፌዴራል ፖሊስ፣ የደህንነት መረብ ኤጀንሲ እና አርቲፌሻል ኢንተለጀንሲ ሃላፊዎች ጋር ዉይይት በማድረግ የማዕድን ፖሊስ ለማቋቋም የመግባቢያ ስምምነት በመፈራረም ወደ ስራ ተገብቷል፡፡ በመሆኑም የሎጂስቲክስ አቅርቦት ግዥ ተጠናቋል (20 ፓትሮል መኪና ግዥ ተፈጽሟል)፣ የቦታዎች ሙሉ መረጃ ማፕ ተደርጓል፣ በቦታው የሚገኙ ኩባኒያዎችና የማዕድናት አይነት መረጃ ለጸጥታ አካላት ተሰጥቷል፡፡ በዚህም መሠረት ኦሮሚያ፣ ቤኒሻንጉል፣ ጋምቤላ፣ ደቡብ ምዕራብ ቦታዎች በክልሉ የጸጥታ ሀይሎች ጸጥታ በማስፈን አምራቾችን ወደ ስራ መመለስ ተችሏል፡፡

• ከአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ጋር በተደረገ ስምምነት ለቀጣይ 10 አመታት በየአመቱ አዳድስ ተማሪዎችን ተቀብሎ የሚያስተምር ሲሆን በዚህ አመት ለ50 ባለሙያዎች ዕድሉ ተሰጥቶ 44ቱ ትምህርታቸውን እየተከታተሉ ይገኛሉ፡፡ በተጨማሪም ለተጨማሪ 6 ባለሙያዎች በተለያዩ የትምህርት ተቋማት የትምህርት እድል ተሰጥቷቸዉ ትምህርታቸዉን እየተከታተሉ የሚገኙ ሲሆን በቀጣይ አጫጭር ስልጠናዎችም ተግባራዊ ይደረጋሉ፡፡

✓ የፀጥታ ችግር በሌለባቸዉ አካባቢዎች የተሰማሩ ኩባንያዎች ያሉባቸዉን ችግሮች በመፍታት ወደ ስራ እንድገቡ የመቀስቀስና ጥብቅ ክትትልና ድጋፍ የማድረግ ስራዎች ተከናዉነዋል፡፡

✓ የቁልፍ ዉጤት አመልካች ተግባራን (KPIs) በሚመለከት ለተፈጠረዉ ችግር ከፕላንና ልማት ሚኒስቴር ጋር በመወያየት ያጋጠሙ ችግሮች ለመፍታት ጥረት እየተደረገ ነዉ፡፡

## 5. ማጠቃለያ

በዘፉ ከተሰሩ የሪፎርም ስራዎች መካከል ምቹ የስራ አካባቢን የመፍጠር ስራ ማለትም የቢሮ ማሻሻል፣ የሠራተኞችን የምግብ አዳራሽና የምግብ ዋጋ የማስተካከል፣ መወገድ ያለባቸዉን ቁሳቁሶች በማስወገድ አካባቢዉን ምቹና ማራኪ የስራ ቦታ የማድረግ፣ በየፍሎሩ መካከለኛ አዳራሾችን ከመገንባት ጎን ለጎን ደረጃዉን የጠበቀ ትልቅ የመሰብሰቢያ አዳራሽ እና የማዕድን ኤግዚቢሽን ጋለሪ የመገንባት፣ ስራዎች እንዲሁም ለክልሎች የተደረገ የባለሙያዎች፣ የቁሳቁስና የሎጂስቲክስ ድጋፍ ስራዎች በስኬት የሚጠቀሱ ናቸዉ፡፡

የድንጋይ ከሰል የክምችት መጠን፣ መገኛ ቦታቸውን በመለየት የጥራት ደረጃውን ከፍ ለማድረግ የሚያስፈልገውን ቴክኖሎጂ እና የሚፈጀውን የኢንቨስትመንት መጠን የሚያሳይ የአዋጭነት ጥናት በመስራት አዋጭነቱን ለማወቅ የተቻለ ሲሆን የአገር ውስጥ ባለሀብቶችን በመጋበዝ የማስተዋወቅ ስራ ተከናውኖ የገንዘብና የቴክኒክ አቅም እንዲሁም ፋብሪካ በመገንባትና በማዕድን ዘርፍ ላይ ልምድ ያላቸውን 8

ኩባንያዎች በመለየት የድንጋይ ከሰል ምርትና ፕሮሰሲንግ ሥራ ፈቃድ መስጠት መቻሉ አበረታች ተግባር ሆኖ ተገኝቷል፡፡

በሲሚንቶ አምራች ኢንዱስትሪ ዘርፍ ኩባንያዎች ያሉባቸዉን ችግሮች በመስክ ጉብኝት ጭምር በመለየትና አምራቾችን በማወያየት ሰፊ ስራ የተከናወነ ሲሆን ኩባንያዎች በጥሬ ዕቃ አቅርቦት ችግር፣ በቴክኒካል ኤክስፐርቶች እጥረት፣ በመለዋወጫ እጦትና በግብይት ሰንሰለቱ ላይ በሚፈጠር ችግር እና መሠል ተግዳሮቶች በሙሉ አቅማቸዉ ማምረት አለመቻላቸዉን የገለፁ ሲሆን የቴክኒካል ኤክስፐርቶችን ችግር ለመፍታት በአገር ዉስጥ ገበያ የማይገኙትን ከዉጭ አገር በማስገባት እንድሰሩ ፈቃድ አግኝተዋል፣ የመለዋወጫ ችግሮችን አስመልክቶ በአገር ዉስጥ ብረታ ብረት አምራቾች ችግሩ እንድቀረፍላቸዉ እና በአገር ዉስጥ የማይገኙትን ደግሞ ከዉጭ እንዲያስገቡ ሁኔታዎችን የማመቻቸት ስራ ተሠርቷል፣ የጥሬ ዕቃ አቅርቦትን በሚመለከት በዘላቂነት ችግሩ የሚፈታበትን ህጋዊ አማራጭ ይዘዉ በመቅረብ ችግሩ እንደሚፈታላቸዉ መስማማት ላይ ተደርሷል፣ በተጨማሪም የግብይት ሂደቱ ላይ ያለዉን አላስፈላጊ ሰንሰለት በማስወገድ ግልጽ የግብይት ሂደት እንዲኖር የሚያደርጉ ተግባራት ተከናዉነዋል፡፡ ይህም የኮንስትራክሽን ዘርፉን ጫና ከመቀነስ አኳያ በስኬት የሚገለፅ ነዉ፡፡

የተለያዩ የማዕድን ማውጫ ቦታዎች ላይ የሚስተዋለዉን የፀጥታ ችግር ለመፍታት ከመከላከያ ሚ/ር፣ ፌዴራል ፖሊስ፣ የደህንነት መረብ ኤጀንሲ እና አርቲፌሻል ኢንተለጀንሲ ሃላፊዎች ጋር ዉይይት በማድረግ የማዕድን ፖሊስ ለማቋቋም የመግባቢያ ስምምነት በመፈራረም ወደ ስራ የተገባ ሲሆን ለዚሁ ስራ አጋዥ የሚሆን የሎጂስቲክስ አቅርቦት ግዥ ተጠናቋል (20 ፓትሮል መኪና ግዥ ተፈጽሟል)፡፡ በተጨማሪም የቦታዎች ሙሉ መረጃ ማፕ ተደርጓል፣ በቦታው የሚገኙ ኩባኒያዎች እና የማዕድናት አይነት መረጃ ለጸጥታ አካላት ተሰጥቷል፡፡ በዚህም መሠረት ኦሮሚያ፣ ቤኒሻንጉል፣ ጋምቤላ፣ ደቡብ ምዕራብ ቦታዎች በክልሉ የጸጥታ ሀይሎች ጸጥታ በማስፈን አምራቾችን ወደ ስራ መመለስ ተችሏል፡፡

የኤክስፖርት ምርቶችን በአይነትና በመጠን በማሳደግ የዉጭ ምንዛሪ ግኝትን ከማሳደግ አኳያ ቀደም ሲል ከሚላኩ ማዕድናት ጎን ለጎን የሶዲየም ብሮማይድ (ብሮሚን) ምርት በዚህ አመት ወደ ገበያ እንዲገባ በማድረግ አበረታች ዉጤት ተገኝቷል፡፡

መዋቅራዊ አደረጃጀቱን ሙሉ በሙሉ በማጠናቀቅ የሰዉ ኃይል ምደባን በአግባቡ ማከናዎን፣ ክልሎችን ይበልጥ በመከታተልና በመደገፍ ዉጤታማነታቸዉ እንዲጨምር ማድረግ፣ አልፎ አልፎ የሚታየዉን የፀጥታ ችግር በመፍታት ማዕድን አልሚዎች ያለስጋት የምርት ስራቸዉን እንዲያከናዉኑ ማድረግ፣ የኩባንያዎችን ችግሮች በማቃለልና ሁሉን አቀፍ ድጋፍ በማድረግ በሙሉ አቅማቸዉ ወደ ስራ እንዲገቡ ማድረግ፣ ኢንቨስትመንትን ሊስቡ የሚችሉ ስራዎችን ማጠናከር፣ ምርትና ምርታማነትን የሚያሳድጉ ስራዎችን በማከናዎን የዘርፍ አፈፃፀምን ዉጤታማነት ማረጋገጥ እንዲሁም የዘርፉን የስራ እድል ፈጠራ በማበረታታት የህብረተሰቡን ተጠቃሚነት ማሳደግ በቀጣይ ትኩረት የሚደረግባቸዉ ጉዳዮች ናቸዉ፡፡

## አባሪ 1

## በ2014 በጀት ዓመት የመጀመሪያ ስድስት ወራት የተሰጡ የማዕድን ኢንቨስመንት ፈቃዶች

| No | Company Name | Nationality | License type | Commodity | Region | new job creation |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | Etenesh melese fanete | Local | Exploration | Opal (Gemstone) | Amhara NRS, N. wello zone , Angot and Gazo woreda | 15 |
| 2 | sino mineTrading Plc | Local | Exploration | Gold and Base metals | SNNPRS, BeNCH ZONE, Tum woreda | 18 |
| 3 | Hora trading | Local | Exploration | Gold | Benishangul NRS, Asosa zone, Menge and Undulu woreda | 31 |
| 4 | SSBTA plc | Local | Exploration | Gemstone | Sidama NRS, Aroresa and Bedesa woreda | 15 |
| 5 | KURMUK GOLDMINE PLC | Foreign | Exploration | Gold and Base metals | Benishangul NRS, Asosa zone,sherkole and Kurmuk woreda | 14 |
| 6 | KURMUK GOLDMINE PLC | Foreign | Exploration | Gold and Base metals | Benishangul NRS, Asosa zone,sherkole and Kurmuk woreda | 14 |
| 7 | MINDI MINING PLC | Foreign | Exploration | Nickel | Oromia | 16 |
| 8 | Tigry Holdings Corp | Foreign | Exploration | Gold and Base metals | tigray NRS, centeral zone, Adwa, enticho and mereb lehe Woreda | 25 |
| 9 | Tigry Holdings Corp | Foreign | Exploration | Gold and Base metals | tigray NRS, north western and centeral zone, asegede tsibla, laelay adiyabo and tsilemti Woreda | 25 |
| 10 | Tigry Holdings Corp | Foreign | Exploration | Gold and Base metals | tigray NRS, north western and centeral zone, asegede tsibla, laelay adiyabo and tsilemti Woreda | 25 |
| 11 | wildsky resources INC | Foreign | Exploration | Gold and Base metals | tigray NRS, centeral zone, asegede tsibla, enticho and mereb lehe Woreda | 10 |
| 12 | san YI Steel plc | Foreign | Exploration | Iron | Oromia NRS, West wellega zone, Gimbi Woreda | 24 |
| 13 | midroc gold mine plc | Foreign | Exploration | Gold and Associated mineral | Oromia NRS, illubabor zone, | 45 |
| 14 | national mining corporation plc | Foreign | Exploration | Coal | Benishangul NRS, Kamashi zone,Kamashi woreda | 9 |
| 15 | Ashute rustom hamdeal | Local | Exploration | Gold | Oromia NRS, Guji zone, Adolana Woreda | 10 |

| No | Company Name | Nationality | License type | Commodity | Region | new job creation |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 16 | sino steel plc | Foreign | Exploration | nikal ,chromit and Associated mineral | Oromia NRS, Guji zone, Oda shkiso Woreda | 17 |
| 17 | sino steel plc | Foreign | Exploration | nikal ,chromit and Associated mineral | Benishangul and oromia NRS, Kamashi and west wellga zone,Agelo mete and boji woreda | 26 |
| 18 | Al Enjaz Agro industry plc | Foreign | Exploration | Gold | Benishangul NRS, Asosa and kamashi zone,bambasi menga and oda godere woreda | 43 |
| 19 | Al Enjaz Agro industry plc | Foreign | Exploration | Gold | Benishangul NRS, Asosa zone, Assosa, bambasi tango SW woreda | 61 |
| 20 | Al Enjaz Agro industry plc | Foreign | Exploration | Gold and related minerals | Oromia NRS, Guji zone, Adolana Woreda | 23 |
| 21 | sun peak ethiopian mining plc | Foreign | Exploration | precious and base metal | tigray NRS, centeral zone, Aberegelle, degua tembien and kolla tembien Woreda | 15 |
| 22 | sun peak ethiopian mining plc | Foreign | Exploration | precious and base metal | tigray NRS, centeral and west zone, mereb lekhe ,laelay adyabo, medebay Woreda | 15 |
| 23 | OROMIA MINING S.C | Local | Mining | Placer Gold | Oromia NRS, Guji zone, Ana sora Woreda | 44 |
| 24 | ALI HAMEL KHADEM | Foreign | Mining | Bromine and Chlorine | Afar NRS, Kilbatti rasu zone, Dalul & Berahale woreda | 118 |
| 25 | BHUMI MINING PLC | Foreign | Mining | Marble | Benishangul Gumuz NRS, Assosa Zone, Oda Biligidilu Woreda | 98 |
| 26 | KRIPTO MINING AND CHEMICALS PLC | Foreign | Mining | Marble | Benishangul Gumuz NRS, Assosa Zone, Oda Biligidilu Woreda | 98 |
| 27 | Zumbara Investment PLC | Local | Mining | Placer Gold | Benishangul Gumuz NRS, Assosa Zone, Oda Biligidilu Woreda | 46 |
| 28 | KURMUK GOLD MINE PLC | Foreign | Mining | GOLD and Base Metal | Benishangul Gumuz NRS, Assosa Zone, Oda Kurmuk Woreda | 740 |
| 29 | ETNO MINING PLC | Foreign | Mining | GOLD and Base Metal | Gambella NRS, Agnuwak Zone, Dima Woreda | 117 |
| 30 | Elnet Thecnology PLC | local | Exploration | Placer Gold | Oromia NRS, Guji zone, Adola and oda shekiso Woreda | 9 |
| 31 | Elnet Thecnology PLC | local | Exploration | Placer Gold | Benishangul Gumuz NRS, Assosa Zone, Banbasi Woreda | 31 |
| 32 | Elnet Thecnology PLC | local | Exploration | Placer Gold | Oromia NRS, Guji zone, Adola and oda shekiso Woreda | 10 |
| 33 | Aleta land and coffee plc | local | Exploration | GOLD and Base Metal | SNNPRS, BeNCH maji ZONE, dizi woreda | 6 |
| 34 | Aleta land and coffee plc | local | Exploration | Iron | Oromia NRS, Jimma zone, olnada Woreda | 24 |

| No | Company Name | Nationality | License type | Commodity | Region | new job creation |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 35 | Kare Mining works PLC | local | Exploration | Placer Gold | Gambella NRS, Agnuwak Zone, Dima Woreda | 7 |
| 36 | OROMIA MINING S.C | local | Mining | caol | | 300 |
| 37 | Sun mining and trading plc | local | Mining | caol | | 136 |
| 38 | Shaka and sons plc | local | Mining | caol | | 300 |
| 39 | National mining corporation plc | Foreign | Mining | caol | | 300 |
| 40 | Rialmine trading plc | local | Mining | caol | | 150 |
| 41 | ET mineral development | local | Mining | caol | | 300 |
| 42 | Elnet technology plc | local | Mining | caol | | 300 |
| 43 | East africa mining corporation plc | local | Mining | caol | | 100 |
| 44 | Shaka and sons plc | local | Exploration | GOLD | Gambella NRS, Agnuwak Zone, abobo and gog Woreda | 11 |
| 45 | GLOBE INVEST FOUR CEMENT IN ETHIOPIA PLC | Foreign | Exploration | Limestone | Oromia National Regional State West Shewa zone Ada Berga and Meta Robi worda | 15 |
| 46 | RAFIQ HUSNI FARIS AL QAB | Foreign | Exploration | GRANITE | | 14 |
| 47 | sino steel plc | Foreign | Exploration | Nickel | | 25 |
| 48 | KENTICHA MINING PLC | Foreign | Mining | tantalem | | |

## በ2014 ስድስት ወራት ዉስጥ በኩባንያና በባህላዊ አምራቾች የቀረበ የወርቅ ምርት

| ተ.ራ | የአቅራቢ ክልል/ኩባንያ ስም | | መለኪያ | የ2014 የስድስት ወራት ዕቅድ | የዕቅድ ክንውን | የዕቅድ አፈፃፀም በመቶኛ |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | ኦሮሚያ ክልል | በባህላዊ | በኪ.ግ | 1710 | 1071.896 | 62.68 |
| | | በኩባንያ (Midroc) | በኪ.ግ | 1370.399 | 1435.925 | 104.8 |
| 2 | ቤንሻንጉል ጉመዝ ክልል | | በኪ.ግ | 1738 | 1074.22 | 61.8 |
| 3 | ጋምቤላ ክልል | በባህላዊ | በኪ.ግ | 800 | 704.972 | 88.12 |
| | | በኩባንያ (እስቴላ) | በኪ.ግ | 20.5 | 13.38 | 65.26 |
| 4 | የደቡብ ምዕራብ ኢትዮጲያ ህዝቦች ክልል | | በኪ.ግ | 233.903 | 143.874 | 61.5 |
| 5 | ሲዳማ ክልል | | በኪ.ግ | 51.5 | 1.936 | 3.7 |
| 6 | አፋር ክልል | | በኪ.ግ | 100.02 | 00 | 00 |
| 7 | አማራ ክልል | | በኪ.ግ | 50.02 | 00 | 00 |
| ድምር | | | | 7000 | 4446.092 | 63.5 |
| ከወርቅ የተገኘ ጥቅል የዉጭ ምንዛሪ በሚ.ዶላር | | | | 514.79 | 272.864 | 53 |